# ተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ፣ ሕጉና አፈጻጸሙ በአማራ ክልል

ሰለሞን ተገኘወርቅ*


## አጽርኦተ-ይዘት

*የአንድ ሀገር የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ውጤታማነት ከሚለካባቸው መመዘኛዎች አንዱ ወንጀል አድራጊዎች 'በአንድ ነጠላ ድርጊት ወይም በተደራራቢ ድርጊቶች' በፈጸሙት የወንጀል ተግባር ልክ ክስ ቀርቦባቸው ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ሲቀጡ ነው፡፡ በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ወንጀል አድራጊዎች አዘውትረው አንድ ነጠላ የወንጀል ድርጊት የሚፈጽሙ ቢሆንም አልፎ አልፎ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጊቶችን "በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ" ወይም "አከታትለው" በተደራራቢነት የሚፈጽሙበት አጋጣሚ እንዳለ ከየእለት ስራችን የምናየው ነው፡፡ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የወንጀል ተግባራት በአንድ ጊዜ ወይም በተከታታይ ተፈጽመው ሲገኙ በመርህ ደረጃ በሁሉም የወንጀል ድርጊቶች ክስ ይቀርብና ወንጀል አድራጊው ጥፋተኛ ሲባል ስለተደራራቢ ወንጀሎች በተቀመጡት "የመደመር" ወይም "የማጠቃለል" የቅጣት አጣጣል መርሆዎች መሰረት ቅጣት ይወሰናል፡፡በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) የወንጀል ህግ ተደራራቢ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የተካተቱ ሲሆን በባለሙያዎች ዘንድ ጽንሰ ሀሳቡን በአግባቡ ያለመረዳት ችግር ይስተዋላል፡፡ በተለይም አንድ ድርጊት ተደራራቢ ለመባል ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች ምንድን ናቸው? ተደራራቢ ወንጀሎች ተደራራቢ ካልሆኑት ወንጀሎች የምንለይበት ስልት ምንድን ነው? እንዲሁም በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ በመደመር ወይም በማጠቃለል መርህ ቅጣት እንዴት ይጣላል? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ በተግባር ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ጥናቱ በወንጀል ህጉ ስለተደራራቢ ወንጀሎች የተቀመጡትን መርሆዎች ይተነትናል፤ በተግባርም በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ክስ እንዴት እየቀረበ እንደሆነና ቅጣት እንዴት እንደሚወሰን ማሳያ የሚሆኑ መዝገቦችንና ሌሎች መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በተግባር ያለውን የአሰራር ጉድለት ያመለክታል፡፡*


*(LLB, LMM in Business and Corporate law) በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ተመራማሪ አገልግለዋል፡፡ አሁን በአብክመ ፍትህ ቢሮ የክልል ዐቃቤ ህግ ሆነዉ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

# 1. የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ-ሀሳብ

የተደራራቢ ወንጀሎችን ጽንሰ ሀሳብ በሚመለከት የወንጀል ሳይንስ /criminal science/ አስተምህሮቶችና ፖሊሲዎች በግልጽ በማስቀመጥ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ያለው ግንዛቤ በበቂ ሁኔታ አድን ባለሙያዎች በቀን ተቀን ስራቸው ጋር በተገናኘ ጽንሰ ሀሳቡን በቀላሉ እንዲረዱት በማድረግ ረገድ ብዙ ርቀት ተሄዷል ለማለት አያስደፍርም[1]፡፡ ይህ ችግር የሚስተዋለው የወንጀል ህጎቻቸውና የወንጀል ፖሊሲዎቻቸው ባላደገበት ሀገሮች ብቻ ሳይሆን የወንጀል ህጎቻቸው ረጅም እድሜ ባስቆጠረውና በወንጀል ሳይንስ ዘርፍም ብዙ ርቀት ሄደዋል በሚባሉ ሀገሮች ጭምር ነው[2]፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጸሀፊዎች እንደሚሉት ከሆነ ቀደም ባሉት ጊዜያት የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ በብዙ ሀገራት የወንጀል ህጎች ውስጥ የተካተተ እንዳነልበር ይጠቁማሉ[3]፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎችን በሚመለከት በወንጀል ህግጋት ውስጥ ከተቀመጠው በላይ በህግ መጽሀፎች እንደተጻፈና በተግባርም በፍትህ አካላት ዘንድ በመዛግብቶች ላይ በስፋት እንደሚያጋጥም ይገለጻል[4]፡፡ ለዚህ የሚቀርበው ምክንያት የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ ውስብስብ እና አስቸጋሪ በመሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ባህሪያቸው ምን ይመስላል? ተደራራቢ ወንጀሎች እንዴት ይፈጸማሉ? ተደራራቢ ወንጀሎች ከነጠላ ወንጀሎች እንዴት ይለያሉ? የሚሉትን ጉዳዮች ህግ አውጭው ቀድሞ ለመረዳት ስለማይቻለው በህግ ማእቀፎች ውስጥ በቀላሉ ለማስቀመጥ ስለሚያስቸግር ነው፡፡ ወደፊትም ቢሆን በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ያለው ግንዛቤ ይበልጥ እያደገ ሊመጣ የሚችለው በህግ መጻህፍቶች በስፋት እየተጻፈ ሲመጣና በተግባርም የፍትህ አካላት በየእለት ስራቸው ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች በመነሳት በአዲስ የሚገኙትን ግኝቶች ወደ ወንጀል ህግ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ነው፡፡

የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ በበቂ ሁኔታ አይደግ እንጂ ወንጀል አድራጊዎች ተደራራቢ የሆኑ የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽሙበት አጋጣሚ እንዳለ የሚታወቅ ነው፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚመጡት አንድ ወንጀል አድራጊ አከታትሎ ወይም በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ /simentannusly/ በሚፈጽማቸው ድርጊቶች በተለያዩ ድንጋጌዎች ስር የተሸፈኑ የአንድ ወይም የሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን መብት በመጣስ ግዙፋዊ

---

[1]Marianne Wells, Sentencing for Multiple Offences in western Australia, the Universtiy of western Australia, crime research center,research report no. 6, 1992, ገጽ 13-15፣ የተወሰደው የካቲት 23/2008 ዓ.ም

[2]ዝኒ ከማሁ

[3]Philippe Graven, An Introduction to Ethiopian Penal code, Haileslasie I Universty, Adiss Ababa,1965, ገጽ 164-166

[4]ዝኒ ከማሁ

ተደራራቢ ወይም ጣምራ ወንጀሎችን ሲፈጽም ነው[5]። ይህ ማለት ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ወይም ተመሳሳይ ያልሆኑ የወንጀል ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ግዙፋዊ መደራረብ የሚያስከትሉ ሲሆን በሌላ በኩል አንድ ህገ ወጥ ድርጊት በተለያዩ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ ያገኙ መብቶችን በመጣስ ጣምራ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ነው[6]። እነዚህ ወንጀሎች የተፈጸሙት በአንድ ድርጊት /in single transaction/ ከሆነ ድርጊቱ ፍጹም ተደራራቢ በሚል የሚታወቅ ሲሆን ወንጀሉ የመጣው በተከታታይ በተፈጸመ ድርጊት /in successive transaction/ ከሆነ አንጻራዊ ተደራራቢ በሚል በጸሀፊዎች ይገለጻል[7]። ተደራራቢ ወንጀሎች የሚፈጸሙት በአንድ ዓይነት መብት/ same right/ ወይም በሚዛመዱ /related right/ ወይም በተለያዩ መብቶች /different right/ ላይ ሊሆን ይችላል።

### 1.1 ተደራራቢ ወንጀሎች በፈጸመ ወንጀል አድራጊ ላይ ቅጣት ከብዶ የሚወሰንበት አግባብ

የወንጀል ህግ ዓላማ በቀዳሚነት ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል እንደሆነና ይህንን ግብ የሚያሳካው በአንድ በኩል ስለወንጀሎችና ስለሚያስከትሉት ቅጣት ከወዲሁ በማሳወቅ ማስጠንቀቅ ሲሆን ማስጠንቀቂያው በቂ ባልሆነ ጊዜ[8] ወንጀል አድራጊዎች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ እንደሆነ ተመልክተናል። ቅጣት ሲጣልም ትክክለኛ፣ ፍትሀዊና ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል[9]። የወንጀል ህግ ዋነኛ መርህ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ለአንድ ድርጊትና ለአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ /mental state/ አንድ ቅጣት የሚለው የሚጠቀስ ነው። ታዲያ በተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ድርጊት በአንድ ወንጀል የማደረግ ሀሳብ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎችን የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ስለምን በሁሉም ድርጊቶች ክስ ይቀርብበታል? ስለምንስ ቅጣቱ ይከብድበታል? የሚል ጥያቄ ብንጠይቅ አንድም ወንጀል አድራጊው ጉዳቱን ያደረሰው ዜጎች በህገ መንግስትና በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶችና ስምምነቶች ላይ ጥበቃ በተደረገላቸው በዜጎች በህይወት የመኖር መብት፣ በአካል ደህንነት መብት፣ በንብረት ጥበቃ መብት እና በሌሎች ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ ስለሆነ ወንጀል

---

[5]የኢትጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ፣ 1996፣ አንቀጽ 60(ሀ፣ ለናሐ)
[6] ዝኒ ከማሁ
[7] Marianne Wells, Sentencing for multiple offences in western australia, the Universty of western Australia crime research center, research no. 6 ገጽ 5 የተገኘው የካቲት 23፣ የተወሰደው www.unswlawjournal.unsw.edu.au/
[8] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ አንቀጽ 1፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006
[9]ዝኒ ከማሁ

አድራጊዎች እነዚህን መብቶች በጣሱ ጊዜ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው[10]። ወንጀል አድራጊዎች ከፈጸሙት ወንጀል ጋር የሚመጣጠን ቅጣት የማይጣል ከሆነ ዜጎች ለመብቶቻቸው ጥበቃ የህግ ዋስትና ስለሚያጡ በግል ፍትህ የመፈለግ /self justice/ አማራጭ ውስጥ እንዲገቡ ይገደዳሉ፤ በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ላይም እምነት ያጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎችን በተደራራቢነት የፈጸመ ወንጀል አድራጊ አንድ ነጠላ ወንጀል ከፈጸመ ወንጀል አድራጊ ጋር ሲነጻጸር አደገኛ ስለሆነና ጥፋቱም በተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ጉዳት ስለሚያስከትል ቅጣቱ ከፍ ሊል ይገባል ከሚል አመክንዮት በመነሳት ነው። ምክንያቱም ቅጣት ሲጣል ምንጊዜም ቢሆን የደረሰውን ጉዳት፣ የተገኘውን ጥቅም፣ የድርጊቱ ተደጋግሞ መፈጸም ግምት ውስጥ የሚገባ ስለሆነ ነው።

በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚጣሉ ቅጣቶች የተመጣጣኝነትን መርህ የሚከተሉ መሆን ይኖርባቸዋል። ቅጣት በአንድ በኩል የወንጀል አድራጊዎችን የመንቀሳቀስ መብት ስለሚገድብ፣ በህይወት የመኖር መብትን ስለሚያሳጣ ወይም በንብረት የመጠቀም መብትን ስለሚነፍግ በቀጥታ ከሰብአዊ መብት ጋር የሚገናኝ ነው። ለዚህም ነው ቅጣት ሲጣል በአንድ በኩል የወንጀል አድራጊውን አደገኛነትና የደረሰውን ጉዳት በሌላ በኩል የወንጀል አድራጊው ሰብአዊ መብት በቅጣት ምክንያት አላግባብ እንዳይገደብ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት ሚዛናዊ እንዲሆን በማሰብ በተደራራቢ ወንጀሎች ጊዜ የመደመርና የማጠቃለል የቅጣት አጣጣል መርሆዎች ተግባራዊ ሆነው ይገኛሉ። የመደመርና የማጠቃለል የቅጣት ዘዴዎች ተግባራዊ የሚሆኑት ምክንያታዊ ያልሆነና ዝቅተኛ ቅጣት እንዳይጣል ለማድረግና ወንጀል አድራጊው በፈጸመው ወንጀል ልክ እንዲቀጣ በማድረግ የቅጣት ቀዳሚ ዓላማ ማስተማር ነው የሚለውን አስተምህሮት ተግባራዊ ለማድረግ ነው። በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲጣል ቅጣቱ የወንጀል አድራጊውን የወንጀለኛነትና የአደገኛነት ባህሪ ማሳየት ይኖርበታል። ገዢው መርህ የሚጣለው ቅጣት ትክክለኛና ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል የሚለው ነው።

---

[10]የወንጀል ህግ አላማ ዜጎች በህግ መንግስትና በሌሎች ሰነዶች ላይ የተሰጣቸውን መብት ለመጠበቅ ሲሆን ወንጀል የሚፈጸመውም በህይወት ላይ፣ በአካል ላይ፣ በንብረት ላይ እንዲሁም በተለያዩ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ እንደሆነ የሚታወቅ ነው።

# 1. ተደራራቢ ወንጀሎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግና ተግባራዊ አፈጻጸሙ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች

## 2.1 ተደራራቢ ወንጀሎች በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት

በሀገራችን የወንጀል ህግ ስርዓት ውስጥ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ተደንግጎ የሚገኘው በ 1949 ዓ.ም ወጥቶ ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ ስራ ላይ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ሲሆን በዚሁ ህግ ተደራራቢ ወንጀሎች ምን ባህሪያት እንዳሏቸውና በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲጣል ፍርድ ቤቶች ሊመሩባቸው ስለሚገቡ መርሆዎች የሚደነግጉ አንቀጾች ተካተውበት ይገኛል[11]፡፡ በዚሁ ህግ ከቁጥር 60-63 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደ ልዩ የቅጣት ማክበጃ የሚወሰዱ መሆናቸውም በዚሁ ህግ በቁጥር 82 ስር የተገለጸ ሲሆን የቅጣት አጣጣሉን በሚመለከት ከቁጥር 189-193 ባሉት ድንጋጌዎች ስር ተካቶ ይገኛል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ስለተደራራቢ ወንጀሎች የሚያወሱ ድንጋጌዎችን ይያዙ እንጂ ድንገጌዎቹ ግልጽነት የጎደላቸውና ተደራራቢ ወንጀሎችን ሰፋ ባለ ሁኔታ አካተው የሚገኙ ባለመሆናቸው በአሰራር ችግር የሚፈጥሩ ነበሩ[12]፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ከአንቀጽ 60-66 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስር ተካተው የሚገኙ ሲሆን ቀድሞ ስራ ላይ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ የነበሩ ክፍተቶችን የሚሸፍንና በአዲስ መልኩ በተደራራቢ ወንጀልነት ሊፈረጁ የሚገባቸውን ተጨማሪ ድርጊቶችን አካቶ ይዟል[13]፡፡ተደራራቢ ወንጀሎች ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሆናቸውም በዚሁ ህግ በአንቀጽ 85 ስር የተገለጸ ሲሆን የቅጣት አጣጣል ስልቱን በሚመለከት ከአንቀጽ 183-187 ስር ባሉ ድንጋጌዎች ስር በዝርዝር ተመልክቶ ይገኛል፡፡

በተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥም ይሁን አሁን ስራ ላይ ባለው የወንጀል ህግ ውስጥ ተደራራቢ ወንጀሎች ምንድን ናቸው የሚለው በትርጉም ደረጃ የተቀመጠ ባይሆንም ተደራራቢ ወንጀሎች የሚባሉት ምን ባህሪያት አሏቸው፣ አንድ ድርጊት ተደራራቢ ወንጀል አስከትሏል ለማለት ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፣ ተደራራቢ ወንጀሎች ተደራራቢ ከማይባሉት ወንጀሎች

[11]የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣ 1949፣ አንቀጽ 60-63፣ ቁጥር 82፣ ቁጥር 189-193

[12]ለምሳሌ ያክል ብንመለከት በ1949 በወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ የተጎጂዎች መደራረብ የተካተተ ስላልነበር በአንድ ድርጊት ብዙ ሰዎች ተመሳሳይ ጉዳት ሲደርስባቸው አንድ ክስ ብቻ ይቀርብ ነበር፡፡ በዚህም ህጉ ኢፍትሀዊ ነው የሚል ትችት ያስተናግድ ነበር፡፡

[13]በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ፣ 1996፣ አንቀጽ 60(ሐ) ስር የተመለከተው በአዲስ የተካተተ ነው፡፡

እንዴት እንደሚለዩና በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲወሰን ፍርድ ቤቶች ሊከተሏቸው ስለሚገቡ መርሆዎች የሚደነግጉ አንቀጾችን እናገኛለን፡፡

## 2.2 የተደራራቢ ወንጀሎች ዓይነት

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚፈጸሙበትንና ባህሪያቸውን መሰረት በማድረግ በዋናነት በሶስት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

***ሀ. ግዙፋዊ መደራረብ* (Material concurrence)**

ግዙፋዊ ተደራራቢ ወንጀል የሚባለው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ሀ) ስር የተመለከተው ሲሆን የዚህ ዓይነት ተደራራቢ ወንጀል በ1949 ዓ.ም ወጥቶ ስራ ላይ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥም ተካቶ እንደነበር ድንጋጌዎችን በማየት መረዳት እንችለላን፡፡ አንድ ወንጀል አድራጊ ተደራራቢነት ያላቸውን ግዙፍ ወንጀሎች ፈጽሟል የሚባለው በአንድ ድንጋጌ ወይም በተለያዩ የወንጀል ሕጉ አንቀጾች ስር የሚያስቀጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን አከታትሎ የፈጸመ እንደሆነ ወይም የፈጸማቸው ተመሳሳይ ድርጊቶች በአንድ የወንጀል ድንጋጌ ስር ተጠቃለው የማይሸፈኑ ሲሆን ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 60(ሀ) ስር እንደተመለከተው ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው የሚከተሉት መመዘኛዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ይሄውም አንድ ወንጀል አድራጊ "ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ፤ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ግዙፍ ወንጀሎችን አከታትሎ የፈጸመ ከሆነ ነው"፡፡ ከእነዚህ መመዘኛዎች የምንረዳው ወንጀል አድራጊው ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ የሚያስከትል ተግባር ፈጸመ የምንለው አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ድርጊቶችን አከታትሎ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ የወንጀል ተግባሮችን የፈጸመ እንደሆነ ነው፡፡ የተፈጸሙት ወንጀሎች በአንድ አንቀጽ ስር የሚሸፈኑ ወይም የማይሸፈኑ እንዲሁም ወንጀሎቹ የተፈጸሙት በአንድ ሰው ወይም በተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ሊሆን ይችላል፤ የሚገኘው ውጤትም ተመሳሳይ ወይም የተለያየ ሲሆን ወንጀል አድራጊው ድርጊቱን የፈጸመው አስቦ ወይም በቸልተኛነት ሊሆን ይችላል[14]፡፡ በዚሁ አንቀጽ ስር "ግዙፋዊ" ውጤት በሚል የተገለጸውና ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ አለ የሚባለው ወንጀል አድራጊው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑት የወንጀል ድርጊቱ ውጤቶች በእጅ የሚዳሰሱና በዓይን የሚታዩ ውጤቶች ስለሚያስከትል ግዙፋዊ ድርጊቶችን በጣምራ የወንጀል ድርጊት አማካኝነት ከሚመጡ በዓይን

[14]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ አንቀጽ 60(ሀ)

ከማይታዩና በእጅ ከማይዳሰሱ የወንጀል ውጤቶችን ለመለየት እንዲረዳ ነው። ግዙፋዊ ተደራራቢ ወንጀሎች ባህሪያቸው ምን እንደሚመስል በምሳሌ ለመመልከት ያክል አንድ ወንጀል አድራጊ የሌላን ሰው ቤት ሰብሮ በመግባት የስርቆት ወንጀል ቢፈጽም፣ ቀጥሎም በቤት ውስጥ በነበረች የ 12 ዓመት ህጻን ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ቢፈጽም ይህ ወንጀል አድራጊ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 665(1) እና በአንቀጽ 627(1) ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸውን ሁለት የተለያዩና በሁለት የተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ግዙፋዊ ውጤት ያስከተለ ወንጀል እንደፈጸመ መገንዘብ ይቻላል። በሌላ ምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ በሀይል የ 'ሀ' ን ሱቅ ቢዘርፍና ወዲያውኑ ከጎረቤቱ የሚኖረውን የ 'ለ' ን መኖሪያ ቤት ቢያቃጥል ግዙፋዊ የወንጀል መደራረብ ስለፈጸመ የወንጀል ህግ አንቀጽ 670/671 እና 494(1) ተጠቅሰው ሁለት ተደራራቢ ክስ ይቀርብበታል። እንዲሁም አንድ ወንጀል አድራጊ በአንድ ቀን በአንድ በተወሰነ ሰፈር ውስጥ አንድ ሰው ቢገድል፣ አንድ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ቢያደርስ፣ በሌላ ሰው ንብረት ላይ የውንብድና ወንጀል ቢፈጽም፣ በሌላ ሰው ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል ቢፈጽም ይህ ወንጀል አድራጊ የሚከሰሰው በ 4 ልዩ ልዩ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ነው። በዚህም መሠረት ለግድያ ወንጀሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 540/539(1-ሀ)፣ ለውንብድና ወንጀሉ አንቀጽ 670/671፣ ለከባድ አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀሉ አንቀጽ 555 እንዲሁም ለመግደል ሙከራው አንቀጽ 27(1) እና 540/539(1-ሀ) ተጠቅሰው ክስ የሚቀርብበትና ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ቅጣቱን ሲጥል የማጠቃለል መርህን በመከተል ቅጣት ሊወስን ይችላል። ተደራራቢ ወንጀል በፈጸሙ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ክስ እንዴት ሊቀርብ እንደሚገባ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ በአንቀጽ 116 ስር አቅጣጫ አስቀምጧል።

ከላይ በአንቀጽ 60(ሀ) ስር ህግ አውጭው ካስቀመጣቸው መመዘኛዎች ውስጥ ግልጽ ያልሆነው ነጥብ ህግ አውጭው **"አከታትሎ"** የሚለውን ቃል ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ማናቸውንም ዓይነት ግዙፍ ወንጀሎችን አከታትሎ ያደረገ እንደሆነ የሚለው የድንጋጌው ማቋቋሚያ ባይኖር ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጊቶችን ተደራራቢ ናቸው አይደሉም የሚለውን መለየት ይቻል ነበርን የሚለው ነጥብ አከራካሪ ነው። "አከታትሎ" (successively) የሚለውን ቃል በሚመለከት በወንጀል ህጉ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጊቶች በተደራራቢነት ተፈጽመዋል ለማለት በመጀመሪያው እና በሚቀጥለው ድርጊት መካከል ያለው የጊዜ መለኪያ አልተቀመጠም። መለኪያውስ ሰዓታት? ቀናት? ሳምንታት? ወራት? ወይስ ዓመታት? የሚለውም የሚያከራክር ነው። ይህን ሀሳብ በሚመለከት

ባለሙያዎች ሁለት አይነት ሀሳቦችን ያስቀምጣሉ። አንዳንድ ባለሙዎች እንደሚሉት ከሆነ አከታትሎ የሚለውን ቃል መረዳት ያለብን ቃሉን በቀን ተቀን ህይወታችን እንደምንረዳው ወንጀል አድራጊው የመጀመሪያውን ወንጀል እንደፈጸመ ወዲያው ሌላ ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ ድርጊቶቹን አከታትሎ ፈጽሟል ሊባል ይችላል በሚል ያስቀምጣሉ[15]። አከታትሎ የሚለው ቃል አንድ ወንጀል አድራጊ የጀመረውን ወንጀል የማድረግ ተግባር ሳያቋርጥ አንድ አይነት ወይም የተለያዩ ወንጀሎችን ፈጽሞ ሲገኝ ነው በማለት ይከራከራሉ። ይህም ሲባል ወንጀል አድራጊው ወንጀል የማድረግ ሀሳቡን ሳይገታ ወንጀሎቹን የፈፀመ እንደሆነ እንጂ ከዚህ ሀሳቡ ከወጣ በኋላ በሌላ ጊዜ እንደገና በአዲስ ሀሳብ ወንጀል ቢፈፅም ቀድሞ ከፈፀመው ወንጀል ጋር አደራርቦ ፈፅሟል ልንል አንችልም፤ ምክንያቱም ወንጀሉን ተደራራቢ እንዲሆን የሚያደርገው በዋናነት የወንጀለኛው ወንጀሎቹን አደራርቦ የመፈፅም እቅድ ነው ሲሉም ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ[16]። ለምሳሌ አንድን ሰው በጥይት ተኩሶ ከገደለ በኋላ ወዲያው ሌላ ሰው ላይ የአካል ጉዳት ቢያደርስ በሁለቱ ወንጀሎች መካከል የድርጊት ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ወንጀሎቹ ተከታትለው ተፈጽመዋል ሊባል እንደሚችል ይጠቁማሉ[17]። ይሄውም ከመጀመሪያው ድርጊት ቀጥሎ የሚፈጸመው ሌላው ድርጊት ከወንጀል አድራጊውና ከማህበረሰቡ አእምሮ ሳይጠፋ በትኩሱ ሲፈጸም አከታትሎ ፈጽሞታል ለማለት ይቻላል የሚል ነው። ይህን ከላይ ያለውን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ አንድ ጸሀፊ አከታትሎ የሚለውን ቃል በምሳሌ ሲገልጽ "ጠላቶቹን ለመጨረስ አቅዶ በ 7 ሰዓት ላይ አቶ ‹ሀ› ን በ 8 ሰዓት ላይ አቶ ‹ለ›ን በ 9 ሰዓት ላይ አቶ ‹መ›ን ቢገድል ይህ ሰው አንድ ዓይነት የሆኑ ሶስት ወንጀሎችን ፈጽሟል"[18] በሚል አስቀምጦታል። በሌላ በኩል ከላይ ከተመለከትነው በተለየ ሁኔታ ሀሳባቸውን የሚሰጡ ባለሙያዎች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ወንጀል አድራጊው የመጀመሪያውን ወንጀል ከፈጸመ በኋላ ይሄው ወንጀል አድራጊ ቀድሞ በፈጸመው ጥፋት ከመቀጣቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ሌላ ወንጀል ቢፈጽም የመጀመሪያው ወንጀል በይርጋ እስካልታገደ ድረስ ወንጀሎቹ ተከታትለው እንደተፈጸሙ ተቆጥሮ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊባሉ ይችላሉ የሚል ነው[19]። ለክርክራቸው ማጣቀሻ የሚያደርጉት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 106 እና 108 ስር የተገለጹትን

---

[15]በሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ የወንጀል የስራ ሂደት ዓቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ ውይይት፣ ሚያዚያ 2/2008 ዓ.ም

[16]ዝኒ ከማሁ

[17]ዝኒ ከማሁ

[18]ጸሀይ ወዳ፣ የወንጀል ህግ መሰረታዊ ሀሳቦች፣ 1994 ዓ.ም

[19]በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የ4ኛ ዙር ቅድመ-ስራ ሰልጣኞች ጋር የተደረገ ውይይት፣ ህዳር 2004 ዓ.ም

ሀሳቦች ነው፡፡ ይሄውም በአንቀጽ 106 ስር የቀላል እስራት ጣሪያ 3 ዓመት ስለሆነና በአንቀጽ 108 መሰረት በሀገራችን የጽኑ እስራት ቅጣት ጣሪያ ከ 25 ዓመት እንደማይበልጥ መደንገጉን ነው፡፡ ለምን ቢባል ወንጀሎቹ ተደራራቢ በሚል ካልተፈረጁ አንድ ግለሰብ በተለያዩ ጊዜያት የፈጸማቸው ወንጀሎች ቢደመሩ ቅጣታቸው በቀላል እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ከ 3 ዓመት ቀላል እስራት እንዲሁም በጽኑ እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ከ 25 ዓመት ሊበልጥ የሚችልበት እድል ስላለ አከታትሎ የሚለውን ቃል ከላይ በተገለጸው መንገድ ካልተረዳነው የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 106 እና 108 ስር ያስቀመጠውን አላማ ማሳካት አይቻልም በሚል ነው[20]፡፡ በአማራ ክልል ባሉ ፍርድ ቤቶችና የዐቃቢያነ መስሪያ ቤቶች በተግባር ያለው አሰራርም የሚያመለክተው ከላይ በሁለተኛ ደረጃ ሀሳባቸውን የሚገልጹ ባለሙዎችን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ ሲሆን ተደራራቢ ወንጀሎችን ለመለየት አከታትሎ የሚለው መመዘኛ ግምት ውስጥ እንደማይገባና የመጀመሪያው ድርጊት በይርጋ ቀሪ እስካልሆነ ድረስ ከሚቀጥለው ድርጊት ጋር ተደራራቢ ይሆናል በሚል ክስ እየቀረበ ውሳኔ እንደሚሰጥ ባለሙዎች ይገልጻሉ[21]፡፡ ባለሙያዎች በየእለት ስራቸው አከታትሎ የሚለውን ቃል ተደራራቢ ወንጀሎችን ለመለየት መመዘኛ በማድረግ ሲከራከሩበት አይታይም፤ ጠበቆችም መቃወሚያ አያቀርቡም፤ ፍርድ ቤቶችም ክርክሮችን ተደራራቢ ናቸው አይደሉም ለማለት አከታትሎ የሚለውን ቃል እንደ መመዘኛ ወስደው ውሳኔ ሲሰጡ አይታይም[22]፡፡

በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 60/ሀ/ መሠረት በተደራራቢነት ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትል ወንጀል የፈጸሙ ወንጀል አድራጊዎች የሚጣልባቸው ቅጣት ከፈጸሙት ወንጀል ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን በማሰብ ህግ አውጭው ያስቀመጠው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በአማራ ክልል ባሉ የዐቃቢያነ ህግ መስሪያ ቤቶች በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት ዐቃብያነ ህጎች የአንቀጽ 60(ሀ)ን ዓላማ በአግባቡ ባለመረዳት አልፎ አልፎ የምርመራ መዛግብቶቹ ወንጀል አድራጊው ተደራራቢ ድርጊት መፈጸሙን እያሳዩ ተደራራቢ ክስ ሳይቀርብ በመቅረቱ ወንጀል አድራጊዎች ባጠፉት የወንጀል ተግባር ልክ ሳይቀጡ እንደሚቀሩ መዝገቦች ያሳያሉ፡፡ ለአብነት ያክል አንድ ወንጀል አድራጊ ግልጽ የሆነ የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ በሚያሽከረክረው ባጃጅ ውስጥ ተሳፍረው በነበሩ 2 ሰዎች ላይ ከባድ ጉዳት አድርሶ ለማምለጥ ሲሞክር በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት እንዳደረሰ የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ የግል ተበዳዮች የህክምና እርዳታ እንዲያገኙ

---

[20] ዝኒ ከማሁ

[21] በሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ በወንጀል የስራ ሂደት ውስጥ ከሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ የጋራ ውይይት መጋቢት 12/2008 ዓ.ም

[22] ዝኒ ከማሁ

ባለማድረጉና በንብረት ላይ ላደረሰው ጉዳት በተደራራቢነት በወንጀል ህግ አንቀጽ 575(2-ለ)ና በአንቀጽ 572(2) መሠረት ክስ ሊቀርብበት ሲገባ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559(2) ተጠቅሶ 2 ክስ ብቻ እንደቀረበበት የክስ መዝገቡ ያሳያል[23]፡፡ በተመሳሳይ 8 ሰዎች በተከሰሱበት የግድያ ወንጀል የሟች ወንድም ወንድሜን ማን መታው እያለ ሟች ወደ ወደቀበት ቦታ ሲሄድ 1ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች የሟችን ወንድም በዱላ በመደብደብ ጉዳት ያደረሱበት መሆኑን የምርመራ መዝገቡ የሚያሳይ ሲሆን 1ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በሟች ወንድም ላይ ለፈጸሙት ቀላል የድብደባ ወንጀል የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(2-ሀ) ተጠቅሶ በወንጀል አድራጊዎቹ ላይ ሁለት ተደራራቢ ክስ መቅረብ ሲገባው 1 ክስ ብቻ እንደቀረበባቸው መዝገቡ ያመለክታል[24]፡፡

### ለ. ጣምራዊ (ሀሳባዊ/ መደራረብ) (የድንጋጌዎች መደራረብ) (notional concurrence)

በወንጀል ህግጋት ውስጥ ተደራራቢ ወንጀል ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የሀሳብ መደራረብ (notional concurrence) የሚባለው ነው፡፡ ጣምራዊ መደራረብ በተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቁጥር 61 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ደግሞ በአንቀጽ 60(ለ) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር አንድ ድርጊት ጣምራ ወንጀሎች አስከትሏል ለማለት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች "በአንድ ድርጊት፤ በአንድ ጊዜ፣ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን መጣስ ወይም፤ በአንድ ጊዜ ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ውጤቶችን የሚያስከትሉ ተግባሮች ተፈጽመው ሲገኙ ነው" በሚል ተቀምጧል፡፡ የዚህ ዓይነት ተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች የሚመጡት በአንድ ነጠላ የወንጀል ድርጊትና በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ /ቸልተኛነት/ በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸው መብቶች ሲጣሱ ነው፡፡ ጣምራ ወንጀሎች ተፈጽመዋል ለማለት በአንድ ድርጊት የተፈጸሙት ወንጀሎች የተለያየ ይዘት እና ባህሪይ ያላቸው በመሆናቸው በተለያዩ ድንጋጌዎች ስር የሚሸፈኑ ናቸው፡፡ ጣምራ ወንጀሎች የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ጥፋተኛ የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት ወንጀል አድራጊው የፈጸመው ድርጊት አንድ ቢሆንም የተለያየ ይዘት እና ባህሪይ ያላቸው ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ በመሆኑ ከአንድ በላይ የሆነ የወንጀል

---

[23]የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መ/ቁ 10030/2006 በዓቃቤ ህግ እና በሞገስ ቦጋለ መካከል የተደረገ ክርክር

[24]የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መ/ቁ. 08519/2006 በ ዐቃቤ ህግና በእነ ዲያቆን መኳንት በላይነህ /8 ሰዎች/ መካከል የተደረገ ክርክር

ማድረግ ሀሳብ አለው ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ወንጀል አድራጊ ድርጊቶችን መደጋገም ሳያስፈልገው በአንድ ድርጊት ብቻ ከአንድ በላይ ጥፋቶችን ለማጥፋት ሀሳብ ያለው በመሆኑ ቅጣቱም በጥፋቱ ልክ መሆን ይኖርበታል በሚል ነው፡፡ በጣምራ የወንጀል መደራረብ ወቅት ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን የሚፈጽመው አስቦ ወይም በቸልተኛነት ሲሆን ለሁሉም ወንጀሎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ /Simultaneously/ ልዩ ልዩ የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸም ጣምራ ወንጀል የሚያስከትለው ውጤት አንድም አንድ ግዙፋዊ ውጤትና ሌሎች ግዙፋዊ ያልሆኑ ውጤቶች ሊያስከትል የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል በጣምራ ወንጀሉ የሚመጡት ሁሉም ውጤቶች ግዙፋዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ባልተመዘገበ የጦር መሳሪያ ተኩሶ ሌላ ሰው ቢገድል በአንቀጽ 60/ለ/ መሰረት የሰው መግደል እንዲሁም ህገ ወጥ መሳሪያ በመያዝ ተደራራቢ ወንጀሎች ፈጽሟል በሚል ክስ ይቀርብበታል፡፡ በዚህ ድርጊት የሰው ግድያ ወንጀሉ ያልተመዘገበ የጦር መሳሪያ ወንጀሉን ስለማይሸፍነው በሁለቱም ድንጋጌዎች ተደራራቢ ክስ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ በህጋዊ ጋብቻ ወስጥ ያለ ሰው ከ 18 ዓመት እድሜ በላይ የሆነች የስጋ ዘመዱን በህዝብ ፊት አስገድዶ ቢደፍር በአንድ ድርጊት 4 ወንጀሎችን እንደፈጸመ እንረዳለን፡፡ በመሆኑም የወንጀል ህግ አንቀጽ 620(1) ለአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ፣ አንቀጽ 652(1) ለአመንዝራነት ተግባሩ፣ አንቀጽ 654 በዘመዳሞች መካከል ለሚፈጸም ግብረ ስጋ ግንኙነት እና አንቀጽ 639(1) ለመልካም ስነ-ምግባር ተቃራኒ የሆነ ተግባርን በአደባባይ መፈጸም ወንጀል በሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ከላይ በምሳሌው የተጠቀሱትን ወንጀሎች ባህሪ ስንመለከት ሁሉም ውጤቶች ከአንድ የወንጀል ድርጊትና ከአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የመጡ ናቸው፡፡ አስገድዶ መድፈር ወንጀሉ ግዙፋዊ ውጤት ያስከተለ ሲሆን ሌሎቹ የወንጀል ውጤቶች ግን ግዙፋዊ ያልሆኑ ናቸው፡፡ ወንጀሎቹ የመጡት በአንድ ድርጊትና በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ሲሆን የወንጀል ህጉ አንቀፅ 620(1) የአስገድዶ መድፈር ጥቃቱን የሚሸፍን ቢሆንም ዝምድናውን፣ የወንጀል አድራጊውን የጋብቻ ሁኔታ፣ እንዲሁም የግብረ ስጋ ግንኙነት በህዝብ ፊት መፈጸምን አይሸፍንም፡፡ በሌላ በኩል በጣምራ ወንጀሎች የሚገኙት ሁሉም ውጤቶች ግዙፋዊ ውጤት የሚሆኑበት አጋጣሚም አለ፡፡ ለምሳሌ አቶ ተጫኔ በቂም በቀል ተነሳስቶ፣ ጨለማን ተገን በማድረግ የ አቶ አጎናፍርን ቤት ለማቃጠል በማሰብ በእሳት ቢያቃጥልና በቃጠሎውም የ አቶ አጎናፍር ትልቅ ልጅ ቢሞትና ትንሹ ልጁ ቀላል የአካል ጉዳት ቢደርስበት እንዲሁም የአቶ አጎናፍር ሚስት ከባድ የአካል ጉዳት ቢደርስባት የተፈጸመው ተግባር አንድ ብቻ /ቤት ማቃጠል/ ቢሆንም ሁሉም የወንጀል ውጤቶች ለዓይን የሚታዩና የሚዳሰሱ ልዩ ልዩ

ግዙፍ ውጤቶች እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 58(1-ለ) መሰረት የአቶ አጎናፍርን ቤት በማቃጠሉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 494(1)፣ የአቶ አጎናፍርን ትልቅ ልጅ ለሞት በማብቃቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 540/539/1-ሀ/፣ በአቶ አጎናፍር ትንሽ ልጅ ላይ ቀላል የአካል ጉዳት በማድረሱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2-ሀ) እንዲሁም በአቶ አጎናፍር የትዳር አጋር ላይ ባደረሰው ከባድ የአካል ጉዳት በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 555/ለ/ መሰረት 4 ተደራራቢ ክስ ሊቀርብበትና ሊቀጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን አቶ ተጫኔ ቤቱን ሲያቃጥል በቤት ውስጥ ሰዎች የሉም በሚል እምነት ከሆነና ሰው ሊኖር እንደሚችል መጠራጠር የሚገባው ከነበረ አስቦ ቤት በማቃጠልና በወንጀል ህግ አንቀጽ 59(1-ለ) መሰረት በቀሪዎቹ ወንጀሎች በቸልተኛነት ሰው መግደልና በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል 3 ክስ ቀርቦበት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች የሚመጡት በሶስት መንገድ ሲሆን አንድም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 66/1-ሀ/ መሰረት ሁሉም ጣምራ ወንጀሎች ታስቦ በሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ወይም በዚሁ ህግ በአንቀጽ 66/1-ለ/ መሰረት የተወሰኑት ወይም ቢያንስ አንዱ ታስቦ በሚፈጸምና ቀሪዎቹ ወንጀሎች በቸልተኛነት ሲፈጸሙ ሲሆን ሌላው በአንቀጽ 66/1-ሐ/ መሰረት ሁሉም ጣምራ ወንጀሎች በቸልተኛነት ሲፈጸሙ ነው፡፡ ወንጀል አድራጊው ጣምራ ወንጀሎቹን የፈጸመው ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማቀድ ወይም ቀድሞውኑ አውቆ በመቀበል ወይም በቸልተኛነት በሆነ ጊዜ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 187 መሰረት ቅጣት አጣጣሉ መሰረታዊ ልዩነት ስለሚያስከትል ጣምራ ወንጀሎቹ የተፈጸሙት ታስቦ ወይም በቸልተኛነት ነውን የሚለውን ነጥብ በጥንቃቄ ማየት ይገባል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ድርጊቶች በአንድ የወንጀል ተግባር ተፈጽመው ጣምራ ወንጀሎች ሊፈጸሙ የሚችሉት በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች ሲሟሉ ሲሆን በተጨማሪም ህግ አውጭው በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ድንጋጌዎችን በማስቀመጥ ድርጊቶቹ በአንድ የወንጀል ተግባር የመጡና በተደራራቢነት ሊያስጠይቁ የሚችሉ ድንጋጌዎችን አመልክቷል፡፡ ባለሙያዎች በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በመመልከት ድርጊቱ ተደራራቢ ወንጀል የሚያስከትል መሆኑ በልዩ ክፍሉ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ ተደራራቢ ክስ የማቅረብ ሀላፊነት አለባቸው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ህግ አንቀጽ 547(1) መሰረት እርጉዝ ሴትን በህገ ወጥ መንገድ እንድታስወርድ በማሰብ ህገ ወጥ ተግባር የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ድርጊቱ የአካል ጉዳት ካስከተለ እንደ ጉዳቱ ከባድነት በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል በአንቀጽ 555/556 በተደራቢነት የሚጠየቅ

ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 349(2) ስር እንደተገለጸው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የመንግስትን ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል እምቢተኛነት ወንጀል ሲሆን እምቢተኛነቱ ዛቻን፣ የሀይል ስራን፣ የእጅ እልፊትን ወይም በጦር መሳሪያ መገልገልና መሳሪያ አንስቶ የመቃጣትን ወይም ሁከትን መፍጠርን አስከትሎ እንደሆነ ጉዳዩን በሚመለከተው ድንጋጌ መሰረት በተደራራቢነት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 441 መሰረት አንድ የመንግስት ሰራተኛ የስራ ግዴታው የሆነውን ተግባሩን እንዳያከናውን በዛቻ በማስገደድ ወይም በሀይል ደርጊት ያሰናከለ ወይም ይህን ግዴታውን እንዲያከናውን ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያስገደደ እንደሆነ የእጅ እልፊቱ ወይም የሀይል ተግባሩ በተባዳዩ ላይ የአካል ጉዳት ወይም የጤንነት ጉድለት ያስከተለ እንደሆነ ድርጊቱ በተደራራቢነት ተፈርጆ አግባብ ባለው ድንጋጌ መሰረት ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በአንቀጽ 444 ስር እንደተመለከተው ጠቋሚዎችና ምስክሮችን በሚመለከት የሚፈጸም ተግባር ወንጀል ሲሆን መረጃ በሰጠው ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ወንጀሉ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም የጤና ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሰረት በተደራራቢ ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በአንቀጽ 587 መሰረት ሴትን መጥለፍ ወንጀል መሆኑ የተደነገገ ሲሆን የጠለፋ ድርጊቱን ወንጀል ተከትሎ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ ድርጊቱ በተደራራቢነት ክስ ሊቀርብ እንደሚገባ በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 2 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ባለሙያዎች ጣምራ የወንጀል ድርጊት መፈጸም አለመፈጸሙን በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) ከተመለከቱት መለኪያዎች በተጨማሪ በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በተደራራቢ ወንጀል ሊያስጠይቁ እንደሚችሉ ህግ አውጭው ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች በጥንቃቂ በማየት ወንጀል አድራጊዎች በፈጸሙት የወንጀል ተግባር ልክ እንዲቀጡ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60/ለ/ መሰረት አንድ ሰው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ተደራራቢ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ በአንቀጽ 65 እና 187/1-2/ ቅጣቱ ከብዶ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ በአማራ ክልል ባሉ የዐቃብያነ ህግ መስሪያ ቤቶችና ፍርድ ቤቶች ያለውን አሰራር ለማሳየት የተወሰኑ መዛግብትን ወስደን ስንመለከት በአንቀጽ 60(ለ) ስር ያለውን መርህ በአግባቡ ባለመረዳት በተግባር ጉድለቶች ይስተዋላሉ፡፡ በአንድ የምርመራ መዝገብ ወንጀል አድራጊዎቹ ሰው ለመግደል በማሰብ የወረወሩት ቦንብ በግል ተበዳይ ላይ ከባድ ጉዳት ያደረሰና በንብረት ላይ ጉዳት የደረሰ

መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ ክስ የቀረበው በከባድ ሰው መግደል ወንጀል ብቻ ነው[25]፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአንድ የምርመራ መዝገብ ላይ ወንጀል አድራጊው የውንብድና ወንጀል እና ተራ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ በወንጀል አድራጊው ላይ የቀረበው ክስ የመግደል ሙከራ ወንጀል ብቻ ሲሆን በውንብድና ወንጀሉ ክስ እንዳልቀረበበት መዝገቡ ያመለክታል[26]፡፡ በተጨማሪ ዐቃቤ ህግ በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) መሰረት በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት የተለያዩ ዓላማ ያላቸው አዋጆችና ድንጋጌዎች ተጥሰዋል በሚል እምነት ወንጀል አድራጊዎችን በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 31(1)ና አንቀጽ 60(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ህጋዊ /የጸና/ የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ በሚያከነውኑ ወንጀል አድራጊዎች ላይ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 43 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መሰረታዊ ምርቶችን በማከማቸት፣ ይዞ በመገኘት፣ በማጓጓዝ፣ በመደበቅ የመሳሰሉ ተግባሮችን በፈጸሙ ወንጀል አድራጊዎች በሁለቱም አዋጆች ስር የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በመጥቀስ ዓቃቤ ህግ 2 ተደራራቢ ክስ ሲያቀርብ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ከሚያየው ፍርድ ቤት እስከ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድረስ ድርጊቱ የተፈጸመው በመነገድ አላማ መሆኑን ዐቃቤ ህግ አላስረዳም በሚልና ድርጊቱ አንድ እስከሆነ ድረስ ድርጊት ፈጻሚው የንግድ ፈቃድ ቢኖረውም ባይኖረውም ድርጊቱ በአንድ አንቀጽ ሊጠቃለል የሚችል በመሆኑ በአንቀጽ 61(1) መሰረት ሊጠቃለል ይገባል በሚል በአንድ ክስ በማጠቃለል አልፎ አልፎ ውሳኔ ሲሰጡ ይስተዋላል[27]፡፡ እንደ ጸሀፊው እምነት ፍርድ ቤቶቹ የሚሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን ወንጀል አድራጊው ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች የማይቀጣ መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት የተፈጸመው ድርጊት በተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ስር የተጠቀሰ ቢሆንም እንኳ አንድ ባህሪ እና ይዘት ኖሮት በአንድ የህግ ድንጋጌ ስር የሚሸፈን ከሆነ ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ ከአንድ በላይ በሆኑ የህግ

---

[25]የሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ፣ የወ/መ/ቁ 59/07፣ ዐቃቤ ህግ እና እነ ጠቅል አየለ /2 ሰዎች/
[26]የሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ፣ የወ/መ/ቁ 206/07 ዐቃቤ ህግ እና ንጉሴ ገነነ
[27]በሰሜን ሸዋ ዞን ንግድ መምሪያ፣ የንግድና ሸማቾች ጥበቃ ዐቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ ውይይት ሚያዚያ 3/2008 ዓ.ም

ድንጋጌዎች ክስ ሊቀርብበትም ሆነ ቅጣት ሊጣልበት አይችልም፡፡[28] ነገር ግን አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ (31-1) የሚያስቀምጠው አንድ ነጋዴ ህጋዊ /የጸና/ የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ ማከናወንን ወንጀል በማድረግ ነጋዲዎች ወደ ንግድ ስራ ከማግባታቸው ፊት ለንግድ ስራ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው እንዲገቡ በማሰብ የተደነገገ ነው፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 43 ስር የተገለጸው መንግስት መሰረታዊ ምርቶች በማለት የሚያስቀምጣቸውን ምርቶች ከመደበኛ የገበያ ስርአት ውጭ ገበያ ለማረጋገት ሲባል መንግስት በሚወስነው የስርጭት ስርአት እንዲሰራጩ ከተፈቀደው ውጭ ሌላ ሰው ሲነግድ፣ ሲያከማች፣ ሲያጓጉዝ ከተገኘ ወንጀል መሆኑ የተደነገገ ሲሆን የክልከላው ዋና ዓላማም እነዚህ ምርቶች በመደበኛው የግብይት ስርዓት እንዲያልፉ ቢደረግ በገበያ ውስጥ እጥረት ሊፈጠር ይችላል ከሚል እምነት ስላለ ይህን ለመከላከል ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም የሁለቱ አዋጆችና በስራቸው የተቀመጡት ድንጋጌዎች አላማ የተለያዩ ስለሆነና የአንዱ አዋጅና ድንጋጌ ይዘት በሌላው አዋጅና ድንጋጌ ስር ስለማይጠቃለል ፍርድ ቤቶች በአንድ ድንጋጌ ስር ይጠቃለላል በሚል የሚሰጡት ውሳኔ ተገቢ ያልሆነና ሁለቱ አዋጆች የወጡበትን አላማ ያላገናዘበ ነው፡፡ ሌላው በፍርድ ቤቶችና በባለሙያዎች ዘንድ ሰፊ ልዩነት ሲፈጥርና የተለያዩ ውሳኔ ሲሰጥ የሚስተዋለው በወንጀል ህግ አንቀጽ 572 ስር በተቀመጠው ድንጋጌ ላይ ነው፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 572(1) ማንም አሽከርካሪ ወይም እግረኛ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብን በመጣስ የሌላን ሰው ህይወት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ አደጋው ባይደርስም እንደሚቀጣ ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር 2 ድርጊቱ በሰው ህይወት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ አግባብነት ያለው ድንጋጌና የተጣሰው የትራፊክ ደንብ ድንጋጌ በተደራራቢነት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ተቀምጧል፡፡ ይህ ድንጋጌ በተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ያልነበረና አሁን ስራ ላይ ባለው የወንጀል ህግ ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የመካተቱ ዋነኛ አላማም አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብን በመጣስ በሰው ህይወት፣ ጤና ወይም ንብረት ላይ ቅርብ የሆነ አደጋ በመፍጠራቸው /potential danger/ ብቻ እንዲቀጡና ከተግባራቸው እንዲታቀቡ ለማድረግ በማሰብ የተደነገገ ነው፡፡ ነገር ግን ቅርብ የሆነ አደጋ ከመፍጠር አልፎ አደጋው እውን ሆኖ በሰው ህይወት፣ ጤና፣ አካል ወይም ንብረት ላይ አደጋ ከደረሰ ክስ እንዴት ይቅረብ በሚለው ዙሪያ በባለሙያዎች ዘንድ ሰፊ ልዩነቶች አሉ፡፡ አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት ወንጀል አድራጊው ግልጽ የሆነ የትራፊክ

[28]Philippe Graven, An Introduction to Ethiopian Penal Law( Article 1- 81), Faculty of Law, Haile Silase I University, Adiss Ababa, Ethiopia 1965, p.165

ደንብ በመተላለፍ የሰዎች ህይወት፣ ጤና ወይም ንብረትን ለአደጋ ካጋለጠ ወንጀል መሆኑ ተደንግጓል፤ ድርጊቱም ጉዳት አስከትሎ ከሆነ የተጣሰው ድንጋጌ መሰረት ተደርጎ ለአደጋ በማጋለጡ የተጣሰው የትራፊክ ደንብና የወንጀል ህግ አንቀጽ 572(1) ተጠቅሶ እንዲሁም ለደረሰው ጉዳት አግባብ የሆነው ድንጋጌ ተጠቅሶ 2 ተደራራቢ ክስ ሊቀርብ ይገባል በሚል ይከራከራሉ[29]፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ሀሳብ የማይስማሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት ለአደጋ ማጋለጥ ወንጀል ተደርጎ የተቀመጠው የወንጀል ድርጊቱ በሰው ህይወት፣ ጤና ወይም ነብረት ላይ ጉዳት ባይደርስም የወንጀል አድራጊው እንቅስቃሴ አደጋ የሚፈጥር በመሆኑ ብቻ ይህንን ድርጊት ለመግታት ድርጊቱ ባይደርስም ወንጀል ተደርጎ ተፈርጇል እንጂ ድርጊቱ አደጋ ከመፍጠር አልፎ ድርጊቱ እውን ከሆነ ሊከሰስ የሚገባው የተጣሰው የትራፊክ ደንብና የደረሰውን ጉዳት የሚሸፍነው ድንጋጌ ተጠቅሶ በአንድ ክስ መሆን ይገባዋል እንጂ አድራጎቱ አደጋ ከመፍጠር አልፎ በሰው ህይወት፣ ጤንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ከደረሰ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) ተጠቅሶ ለአደጋ ማጋለጥ በሚል በተደራራቢነት ክስ ይቅረብበት ማለት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) እና በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር 2 ስር ህግ አውጭው ያስቀመጠውን አላማ አለመገንዘብ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ በተግባርም በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች እንደሚስተዋለው ዐቃቤ ህግ 2 ተደራራቢ ክስ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ ከደረሰ ክስ ሊቀርብ የሚገባው ጉዳቱን በሚመለከተው ድንጋጌ ብቻ እንጂ በደረሰ ጉዳት ላይ ለአደጋ ማጋለጥ በሚል በተደራራቢነት ክስ ማቅረብ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ በ 1 ክስ ብቻ ውሳኔ ሲሰጡ ይስተዋለለል[30]፡፡ ይህን ነጥብ በሚመለከት የጸሀፊው እምነት ግልጽ የሆነ የትራፊክ ደንብ ተጥሶ የሰውን ህወት፣ ጤንነት ወይም ንብረት ላይ አደጋ ደርሶ ከሆነ ወንጀል አድራጊው ሊጠየቅ የሚገባው የተጣሰው የትራፊክ ደንብና አግባብነት ባለው የወንጀል ህጉ ድንጋጌ ተጠቅሶ በ 1 ክስ ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) ስር ያስቀመጠው ክልከላ አሽከርካሪዎች አደጋ ባያደርሱም ለአደጋ ማጋለጣቸው ብቻ ወንጀል እንዲሆን በማሰብ የተደነገገ ነው፡፡ ነገር ግን ለአደጋ ከማጋለጥ አልፎ አደጋው ከደረሰ የደረሰውን አደጋ የሚመለከተው ድንጋጌ ብቻ ተጠቅሶ ክስ መቅረብ አለበት የሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል የአሽከርካሪው አድራጎት በተወሰኑ ሰዎች ላይ ጉዳት አድርሶ በሌሎች ላይ ለአደጋ አጋልጦ ካለፈ ግን በወንጀል አድራጊው ላይ ለአደጋ በማጋለጥና አደጋ በማድረስ በ 2 ተደራራቢ ክስ

[29]በባህር ዳር ከተማ ከግንቦት 29-30/2008 ዓ.ም በአማራ ክልል ከሁሉም ዞኖች ከመጡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞችና የዞን ዐቃብያነ-ህጎች ጋር የተደረገ የጋራ ውይይት

[30]በደብረ ብርሀን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል የስራ ሂደት ውስጥ ከሚሰሩ ዳኞች ጋር የተደረገ ውይይት፣ መጋቢት 4/2008 ዓ.ም

ሊቀርብበት እንደሚገባ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ለምሳሌ አንድ አሽከርካሪ በፍጥነት ሲያሽከረክር መኪናው በመገልበጡ በ 3 ሰዎች የአካል ጉዳት ቢደርስና በመኪናው ላይም ጉዳት ደርሶ በሌሎች ተሳፍረው በነበሩ 7 ሰዎች ላይ ጉዳት ሳይደርስ ቢቀር ተደራራቢ ወንጀሉ በወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ለ) መሰረት በአንድ ድርጊት የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች የተጣሱ ስለሆነ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የወንጀል ህጉ አንቀጽ 559(2) ተጠቅሶ 3 ክስ፣ ለንብረት ጉዳቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 856 ተጠቅሶ 1 ክስ እንደሁም 7 ሰዎች ለአደጋ የተጋለጡ ስለሆነ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 572(1) ተጠቅሶ 7 ክስ በድምሩ 11 ክስ ይቀርብበታል ማለት ነው፡፡

**ሐ. የተጎጂዎች መደራረብ (Victims concurrence)**

ይህ ዓይነቱ ተደራራቢ ወንጀል በወንጀል ህጋችን በአዲስ መልኩ የተካተተ የወንጀል ተደራራቢ ዓይነት ሲሆን በ 1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ አልነበረም፡፡ ይህ አይነት ተደራራቢ ወንጀል የተጎጂዎች መደራረብ በሚል ይጠራል። ምክንያቱ ደግሞ ድንጋጌው የሚያተኩረው አንድ ድርጊት በብዙ ሰዎች መብት ላይ ተመሳሳይ ጉዳት ስለሚያስከትል ነው፡፡ በአንቀጽ 60(ሐ) ስር የተቀመጠው መመዘኛ "በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት፤ አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ፤ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ፤ ተመሳሳይ ዓይነት ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ፣ የተጣሰው አንድ የህግ ድንጋጌ ሲሆን፣ የደረሰው ጉዳት ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት /ጥቅም/ ላይ ሲሆን፣ ጉዳቱም አንድ አይነት መሆን ይኖርበታል፡፡ ነገሩን በምሳሌ ለመግለጽ ያክል አንድ አሽከርካሪ ከላይ የጫነው ጎማ በአግባቡ ባለመታሰሩ ወድቆ ሁለት ሰዎች ላይ ጉዳት ቢያደርስ ድርጊቱ አንድ ነጠላ ድርጊት ቢሆንም በአንድ ድርጊት በሁለት ሰዎች መብት ላይ ጉዳት ስላደረሰ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559(2) ተጠቅሶ 2 ተደራራቢ ክስ ይቀርብበታል ማለት ነው፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ ሰው ለመግደል አስቦ በቆሙ ሰዎች ላይ ቦንብ ወርውሮ ሁሉንም ቢገድል ድርጊቱ በአንቀጽ 60(ሐ) ስር የሚያርፍ ሲሆን የተፈጸመው ወንጀል በብዙ ሰዎች ላይ የሰው መግደል ወንጀል ስለሆነና ተመሳሳይ ጉዳት በመሆኑ በወንጀል አድራጊው ላይ 1ኛ፣ 2ተኛና 3ተኛ ክስ በሚል በሞቱት ሰዎች ቁጥር ልክ የሰው መግደል ወንጀል ክስ ይቀርባል ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነት ተደራራቢ ወንጀል በ 1949 በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ስላልነበረ የተጎጂዎች መደራረብ ሲያጋጥም ለሁሉም ወንጀሎች አንድ ክስ ብቻ ይቀርብ ነበር፡፡ አሁን ስራ ላይ ያለው የወንጀል ህግ በቀድሞ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ይስተዋል

የነበረውን ችግር ስለፈታ በተጎጂዎቹ ቁጥር ልክ ክስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ውስጥ ይህ አይነት ተደራራቢ ወንጀል እንዲካተት የተደረገበት ምክንያት አንድ ወንጀል አድራጊ በብዙ ሰዎች መብት ላይ በአንድ ጊዜ ላደረሰው ጉዳት በተደራራቢ ወንጀል ሳይጠየቅ እንደ ነጠላ ድርጊት ተቆጥሮ ለአንዱ ድርጊት ብቻ የሚቀጣ ከሆነ ዜጎች በህገ መንግስት የተደረገላቸውን በህይወት የመኖር መብት፣ የአካል ደህንነት መብት፣ የንብረት መብት ጥበቃ ዋስትና አለመስጠት ነው እንዲሁም ቅጣት ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚለውን መርህም የሚጻረር ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥም ብዙ ወንጀሎች የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ላይ የሚሰጠው የህሊና ፍርድ ቅጣቱ በቂ ስለማይሆን ማህበረሰቡ በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል በጣምራ የወንጀል ተግባር አንድ ወንጀል አድራጊ የተወሰኑትን ወንጀሎች አስቦና ሌሎቹን በቸልተኛነት ሲፈጽም ቅጣቱ እንዲከብድ ተደርጎ በአንድ ድርጊት ብዙ ሰዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ወንጀል የፈጸመ ወንጀል አድራጊ አንድ ክስ ብቻ ቀርቦበት ቅጣቱ እንዲቀል የሚደረግ ከሆነ ቅጣት ***የእድል ጉዳይና አመክንዮት የሌለው*** ይሆናል ከሚል እምነት ነው፡፡ ለምሳሌ ‘ሀ’ ሚስቱን የወሸመበትን ‘ለ’ ን ለመግደል በማሰብ በቤት ውስጥ ተኝተው እንዳለ ጥይት በመተኮስ ‘ለ’ ን ቢገድልና በራሱ ሚስት ላይ የአካል ጉዳት ቢያደርስ በአንቀጽ 60(ለ) መሰረት ጣምራ ወንጀል ስለፈጸመ በሰው መግደልና በአካል ጉዳት ማድረስ 2 ክስ ቀርቦበት ከፍተኛ ቅጣት መቀጣት አለበት እንደ ማለት ሲሆን ነገር ግን ሁለቱም ሰዎች ሞተው ቢሆን ኖሮ አንድ ክስ ይቀርብበትና በአንድ ሰው መግደል ወንጀል ብቻ ዝቅተኛ ቅጣት ይቀጣል ማለት ነው፡፡ በሌላ ምሳሌ ቦንብ ጥሎ አራቱንም ሰዎች መግደልና ቦንብ ጥሎ 2ቱን መግደልና 2ቱ ላይ የአካል ጉዳት ማድረስን በሚመለከት ቅጣቱ የሚቀለው 4ቱንም በገደለው ላይ ሲሆን 2ቱን ገድሎ በ2ቱ ላይ የአካል ጉዳት ያደረሰው ወንጀል አድራጊ ቅጣት ይከብድበታል እንደ ማለት ሲሆን ቅጣት ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ከሚለው መርህ ጋርም አብሮ አይሄድም፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) ስር እንደተመለከትነው በአንድ ድርጊት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ ተመሳሳይ የሆነ ጉዳት በደረሰ ጊዙ በተጎጂዎቹ ሰዎች ቁጥር ልክ ክስ መቅረብ እንዳለበት ተመልክተናል፡፡ ይህ መርህ ሲሆን የዚህ መርህ ልዩ ሁኔታ ህግ አውጭው በወንጀል ህግ አንቀጽ 543/3/ ስር ያመለከተው ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የአሽከርካሪነት ተግባሩን በአግባቡ ባለመወጣት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ ድርጊቱን በራሱ የቅጣት ማክበጃ አድርጎ በመውሰድ

አንድ ክስ እንዲቀርብና ቅጣት እንዲጣል ህግ አውጭው በልዩ ሁኔታ እንዳስቀመጠ ማየት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በአዋጅ ቁጥር 909/2007 ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ስደተኞችን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ በአንቀጽ 6 ስር እንዳመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ተጎጂ የሆኑት ሰዎች ቁጥር በስፋትና በብዛት በሆነ ጊዜ ቅጣቱ ከብዶ እንደሚወሰን ያሳያል፡፡ ይህ አዋጅ ወጥቶ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የወንጀል ህግ አንቀጽ 98 ተጠቅሶ ክስ ይቀርብ በነበረበት ጊዜ ክሱ ይቀርብ የነበረው ጉዳት በደረሰባቸው ሰዎች ቁጥር ልክ እንደነበር የውሳኔ መዛግብቶች ያሳያሉ፡፡ አሁን በተግባር እየተሰራ ያለው የድርጊቱ ሰለባ /ተጎጂዎች/ ቁጥር ሁለትና ከዚያ በላይ በሆነ ጊዜ አንድ ክስ ብቻ በማቅረብ ሲሆን ድንጋጌው በራሱ ቅጣት ማክበጃ ሆኖ ተደንግጓል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ አዋጅ ጋር በተገናኘ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የሚያመለክተው በህገ ወጥ መንገድ ሰዎችን የሚያዘዋውሩ አዘዋዋሪዎችን ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር እንደተገለጸው ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን በሚመለከት ሌሎች የተለያዩ አካላት ሊሳተፉ እንደሚችሉ በማመን ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን በገንዘብ፣ በሀሳብ፣ በተሽከርካሪ፣ የመኖሪ ቤት በማቅረብና በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላትና በወንጀሉ የተሳተፉ አካላት በህገ ወጥ የሰዎች ማዘዋወር ወንጀል ሊጠየቁ እንደሚገባ አዋጁ ያመለክታል፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ቅጣቱ ከብዶ የሚወሰነው በአዘዋዋሪዎቹ ላይ ብቻ ሲሆን የተሽከርካሪና ሌሎች ድጋፍ ባደረጉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ክስ የሚቀርበው የወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) በሚያስቀምጠው መሰረት በተጎጂዎቹ ቁጥር ልክ ነው ወይስ በአዋጁ አንቀጽ 6 መሰረት ነው የሚለው ግልጽ አይደለም፡፡ ይህን ነጥብ በሚመለከት ባለሙዎች ሁለት አይነት ሀሳቦችን ያስቀምጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንደሚሉት በአዋጁ አንቀጽ 6 ስር በከባድ ሁኔታ ክስ ሊቀርብባቸው የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 3 እና 5 ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኝ በአዘዋዋሪዎቹ ላይ ብቻ እንደሆኑ በህጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በአዋጁ የትርጉም ክፍል ላይ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተግባርን የሚረዱ ሰዎች በህገ ወጥ አዘዋዋሪ ሊጠየቁ እንደሚችሉ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን እነዚህ በህገ ወጥ ማዘዋወር ተግባሩ የተሳተፉ ወንጀል አድራጊዎች ክስ እንዴት ሊቀርብ ይችላል የሚለውን ህግ አውጭው በዝምታ ማለፉ ክፍተት የፈጠረ ቢሆንም በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 6 ስር በተጠቀሰው መሰረት ክስ ይቅረብባቸው ማለት ግን ከህግ አውጭው ሀሳብ መራቅ ነው በማለት ይከራከራሉ[31]፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች እንደሚሉት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) ስር የተቀመጠው ጠቅላላ መርህ ስለሆነ ሌሎች

[31]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 29 የተጠቀሰው

አዋጆች በግልጽ የተለየ የክስ አቀራረብ እንዲኖር እስካላስቀመጡ ድረስ በህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር ላይ ተሳታፊ በሆኑ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ክስ ሊቀርብ የሚገባው በተጎጂዎቹ ቁጥር ልክ ሊሆን እንደሚገባ ያስቀምጣሉ[32]፡፡ በሌላ በኩል ይህን ሀሳብ የሚቃወሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት ህገ ወጥ ሰዎች ዝውውርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ልዩ አዋጅ ስለሆነ እና የዚሁ ህግ አንቀጽ 6 ላይ አዘዋዋሪዎችን በሚመለከት የተጎጂዎቹ ቁጥር ብዙ በሆነ ጊዜ የቅጣት ማክበጃ የቀረበው በማዘዋወሩ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለተሳተፉ ወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚ መሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን በሚመለከት አዋጁ ልዩ ህግ ስለሆነ ወደ ወንጀል ህ ጠቅላላ መርህ መሄድ አይገባም ሲሉ ክርክራቸውን ያቀርባሉ[33]፡፡ እንደ ጸሀፊው እምነት በአዋጁ አንቀጽ 6 ላይ ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን የተፈለገው አዘዋዋሪዎችን የሚመለከት መሆኑ በግልጽ የተቀመጠ ስለሆነ ሌሎች በህገ ወጥ ዝውውር ተግባሩ ውስጥ ተሳታፊ ሆነው የሚገኙ ወንጀል አድራጊዎች በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60(ሐ) መሰረት በተጎጂዎች ቁጥር ልክ ክስ ቀርቦ ሊቀጡ ይገባል የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም የወንጀል ህጉ ላይ የተመለከቱ መርሆዎች በግልጽ በልዩ ህግ በተለየ መንገድ እንዲፈጸም ካልተመለከተ በስተቀር በወንጀል ህጉ ውስጥ የተቀመጡት መርሆዎች ጠቅላላ መርሆዎች ስለሆኑና ወንጀል ነክ ላላቸው አዋጆች ሁሉ ተፈጻሚ ስለሆኑ ልዩ አዋጆች ክፍተት በሚኖራቸው ጊዜ ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል ከሚል መነሻ ነው፡፡

የወንጀል ህግ አንቀፅ 60/ሐ/ን በሚመለከት በተግባር በዐቃብያነ ህግ መስሪያ ቤትና በፍርድ ቤቶች በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት በድንጋጌው ስር በተመለከተው መርህ መሠረት በተበዳዮቹ ቁጥር ልክ በተደራራቢነት ክስ መቅረብ እየተገባው ባለሙያዎች ይህን ድንጋጌ በአግባቡ ባለመረዳት አልፎ አልፎ በተጎጂዎች ቁጥር ልክ ክስ አለማቅረብ፤ ክስ ቢቀርብም ፍርድ ቤቶች በአንድ ክስ የሚጠቃለል ነው በማለት ውሳኔ እንደሚሰጡ መዝገቦች ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ በአንድ የተሽከርካሪ አደጋ ወንጀል ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ሐ) ን መሰረት በማድረግ በ 6 ሰዎች ላይ በደረሰው የአካል ጉዳት ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559(2) ስር የተመለከተውን በመጥቀስ 6 ክስ ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ሁሉም ድርጊት በአንድ ክስ ሊጠቃለል ይገባል በሚል በአንድ ክስ አጠቃሎ ውሳኔ

[32] ዝኒ ከማሁ
[33] ዝኒ ከማሁ

ሰጥቷል[34]፡፡ በተመሳሳይ በአንድ የማታለል ወንጀል የማታለል ወንጀሉ የተፈጸመው በሁለት የግል ተበዳይዎች ላይ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ የቀረበው ክስ አንድ ብቻ እንደሆነ መዝገቡ ያሳያል[35]፡፡ በሌላ መዝገብ ወንጀል አድራጊዎች በአንድ ድርጊት በተለያዩ ሰዎች መብት ላይ ተመሳሳይ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ የሚያመለክት ቢሆንም አንድ ክስ ብቻ ቀርቦ ውሳኔ እንደተሰጠ መዝገቡ ያሳያል፡፡[36]

## 2.3 ፍጹም ተደራራቢ ያልሆኑ ወንጀሎች (imperfect concurrence)

ከወንጀል ህግ መርሆዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው አንድ ወንጀል አድራጊ ሊቀጣ የሚገባው ወንጀል ለመፈጸም ባለው ሀሳብ ልክ ነው የሚለው ነው፡፡ የወንጀል አድራጊው ወንጀል የመፈጸም የሀሳብ ሁኔታ የሚረጋገጠው ደግሞ በወንጀል አድራጊው የወንጀል ድርጊት የተጣሱ መብቶች ወይም ህገ ወጥ ድርጊቶችና ወንጀል አድራጊው ድርጊቱን በሚፈጽምበት ጊዜ ያደረገውን እንቅስቃሴ ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣመር በሚገኝ የፍሬ ነገር ትንታኔና ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 60 ስር የተመለከተው መርህ አንድ ወንጀል አድራጊ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ግዙፋዊ ወይም ጣምራ ወንጀሎችን ሲፈጽም በተደራራቢ ወንጀሎች ተጠያቂ የሚሆንበትን አግባብ ሲሆን በዚሁ ህግ በአንቀጽ 61 ስር የተደነገገው ደግሞ የተወሰኑ ድርጊቶች /ወንጀሎች/ በባህሪያቸው ተደራራቢ ቢመስሉም ተዳራራቢ ሊባሉ የማይችሉ የተደራራቢ ወንጀሎች ልዩ ሁኔታ /exception/ በመሆን የተቀመጡ ናቸው፡፡ አንዳንድ የወንጀል ድርጊቶች ከላይ ሲታዩ በተለያዩ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸው መብቶችን የሚጥሱና የተደራራቢ ወንጀሎች ባህሪ ያላቸው ይመስላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉንም ድርጊቶች አጠቃሎ የሚይዝ አንድ ድንጋጌ ሲኖር ወይም ድርጊቶቹ ቢደጋገሙም በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸሙ ናቸው የሚያስብል ምክንያት በተገኘ ጊዜ ወንጀል አድራጊው

---

[34]በሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ የሀገረ ማሪያም ወረዳ የወ/መ/ቁ. 241/2008፣ በተከሳሽ ሰይፈ ገብረየስና በዐቃቤ-ህግ መካከል በተደረገ ክርክር ዐቃቤ-ህግ 7 ክስ ያቀረበ ሲሆን ወንጀሉ ከ1-6 ያሉት ክሶች በቸልተኛነት በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል አንቀጽ 559(2) ሲሆን የሰጠው ውሳኔ ከ1-6 ያሉት ክሶች በአንድ ክስ የሚጠቃለሉ ናቸው በማለት አንድ ክስ እንዲሆን ብይን በመስጠት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

[35]የደቡብ ወሎ ዞን ፍትህ መመሪያ፣ የወ/መ/ቁ 270/2007 ዓቃቤ ህግና እነ ፈንታ በላይ

[36]የምዕራብ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ የወንጀል የወ/መዝ/ቁ/ 033240 ዐቃቤ-ህግና እስከዚያ ጥላሁን፣ የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መዝ/ቁ/መ/ቁ/ 09324 ዐቃቤ-ህግ እና ሞላ ታደሰ፣ የወ/መ/ቁ/ 09647 ዐቃቤ-ህግ እና አስማማው ሞገስ፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መ/ቁ/ 209/07 ዐቃቤ-ህግና መሀመድ ይርጋ፣ የአዊ ብሄረሰብ ዞን ፍትህ መምሪያ የወ/መዝ/ቁ.134/07 ዐቃቤ-ህግና አስፋው አፈረ

ጥፋተኛ የሚባለው ሁሉንም ድርጊቶች አጠቃሎ በሚይዝ በአንድ ድንጋጌ ብቻ ሊሆን እንደሚገባ የሚጠቁሙ የወንጀል ህግ መርሆዎች አሉ፡፡
በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ውስጥ ተደራራቢ ሊባሉ የማይገባቸው ድርጊቶች የተመለከቱት በአንቀጽ 61ና 63 ስር ነው፡፡ በአንቀጽ 61 ስር ተደራራቢ ያልሆኑ ድርጊቶች በሶስት ምክንያቶች ሊመጡ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊባሉ ከማይገባቸው ተግባሮች ውስጥ አንዱ በአንቀጽ 61(1) ስር የተጠቀሰው ሲሆን በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሰረት አንድን ድርጊት ተደራራቢ ያልሆነ በሚል ለመፈረጅ የተቀመጡ መመዘኛዎች *"በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ፤ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች፤ የተደረጉት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን፤ ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ" ከሆነ ነው በሚል የተቀመጠ ነው፡፡* ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው መሰረታዊ ነጥብ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ ድርጊቶች በሚፈጸሙ ጊዜ ተደራራቢ ይባላል አይባልም ለሚለው መልስ የሚያግዘን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑና የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙት በአንድ መብት ላይ ነውን? ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን የፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ /ቸልተኛነት/ ነውን? ሁሉም የተፈጸሙት ድርጊቶች በተለያዩ ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ የተደረገላቸው ቢሆኑም ሁሉንም መብቶች አጠቃሎ ሊሸፍን የሚችል አንድ ድንጋጌ አለን? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥምረት (comulatively) መመለስ ከተቻለ ወንጀል አድራጊው ስለሌሎቹ ድርጊቶች ጭምር በተደነገገው በአንድ ድንጋጌ የሚቀጣ ይሆናል፡፡ በወንጀል ህጋጋት ውስጥ የተለያዩ ድንጋጌዎች አንድን መብት ወይም የተዛመዱ መብቶችን ወይም ተመሳሳይነት ባህሪ ያላቸውን ህገ ወጥ ድርጊቶች ለመጠበቅ /ለመከላከል/ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በየራሳቸው የቆሙት አንድን መብት ለመጠበቅ ቢሆንም አንዳንድ ድንጋጌዎች የሌላው ድንጋጌ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር (ingredient element) ሆነው የሚገኙበት ጊዜም አለ፡፡ እንደዚህ ዓይነት የተዛመዱ ተደራራቢ ወንጀሎች በተፈጸሙ ጊዜ ህግ አውጭው የወሰደው አማራጭ ወንጀል አድራጊውን በሁሉም ድንጋጌዎች ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ በአንዱ ድንጋጌ ስር ያሉት ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ለሌላው ድንጋጌ እንደ ማክበጃ ተቆጥረው በወንጀል ህግ አንቀጽ 185/2/ መሰረት ቅጣቱ መክበድ እንደሚገባው ነው፡፡ በእርግጥ በገሀዱ ዓለም ተደራራቢ ወንጀሎች የሆኑትን ተደራራቢ ከማይሆኑት መለየት ሁልጊዜም ቀላል ስራ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተደራራቢ የሆኑትን ተደራራቢ ከማይሆኑት ተግባራት ለመለየት የሚያስችል ሳይንሳዊ ወይም ሂሳባዊ ስሌት ማስቀመጥ ስለማይቻልና ጥቂት ምሳሌዎችን በማሳየትም ተደራራቢ የሆኑትንና ተደራራቢ

ያልሆኑትን መለየት ስለሚያስቸግር ነው፡፡ በመሆኑም ተደራራቢ የሆኑትን ወንጀሎች ተደራራቢ ካልሆኑት ለመለየት ዓቃብያነ ህጎች፣ ዳኞች፣ ጠበቆችና ሌሎች ባለሙያዎች የተፈጸሙት ብዙ ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን ወይም ድርጊቶቹ ቢደጋገሙም በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸሙ መሆናቸውን በድርጊቱ ውስጥ ካሉ ፍሬ ነገሮች በመረዳትና በመተንተን እንደ ጉዳዮቹ ሁኔታ መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡

በወንጀል ህግ አንቀጽ 61(1) ስር የተቀመጠውን መርህ በምሳሌ ስንመለከት በወንጀል ህግ አንቀጽ 665 እና 670/671 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በንብረት መብት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመጠበቅ የተደነገጉ ናቸው፡፡ ታዲያ አንድ ወንጀል አድራጊ የሌላን ሰው ንብረት ያለባለቤቱ ፈቃድ በመውሰድ ተግባር ቢጠረጠር ወንጀል አድራጊው የሚከሰሰው በስርቆት ወይም በውንብድና ወንጀል ነው፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ በስርቆትና በውንብድና ወንጀሎች ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱ የተፈጸመው በአንድ በህግ ጥበቃ በተደረገለት መብትና በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ በመሆኑ ነው፡፡ መብቱ በሁለቱም ድንጋጌዎች ስር ጥበቃ ተደርጎለት ይገኛል፡፡ ተጠርጣሪው ንብረቱን የወሰደው ሐይል ተጠቅሞ ከሆነ እንደ ነገሩ ሁኔታ በአንቀጽ 670/671 የሚጠየቅ ሲሆን ድርጊቱን የፈጸመው ሀይል ሳይጠቀም ከሆነ በአንቀጽ 665(1) በስርቆት ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በስርቆት ወንጀል ጊዜ የመብት ጥሰት የሚደርሰው በንብረት መብቱ ላይ ብቻ ነው፡፡ በአንጻሩ በውንብድና ወንጀል ጊዜ ወንጀሉ የሚፈጸመው በአካል ደህንነት (በህይወት የመኖር መብትና) በንብረት መብት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በውንብድና ወንጀል ውስጥ የአካል ደህንነት መብት (የህይወት) መብትና የንብረት መብት ተቀላቅለው የሚገኙ ሲሆን ድርጊት ፈጻሚው የሚጠየቀው የሁለቱንም የመብት ጥሰጦች አጠቃሎ በሚይዘው በአንቀጽ 670/671(1-ለ) በውንብድና ወንጀል ብቻ እንጂ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 556 /555/ እና 540/539(1-ሀ)/ እና በአንቀጽ 665(1) በተደራራቢነት የሚከሰስበት አግባብ አይኖርም፡፡ በሌላ ምሳሌ በአስገድዶ መድፈር የወንጀል ተግባር ውስጥ የመንቀሳቀስ መብትን መገደብና አስገድዶ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ድርጊቶች ተቀላቅለው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ድርጊቶች ለየብቻቸው ሲታዩ ሁለት ድርጊቶች ቢሆኑም የመንቀሳቀስ መብት መገደብ ለአስገድዶ መድፈር ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ስለሆነና የመንቀሳቀስ መብት ሳይገደብ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ስለማይፈጸም ወንጀል አድራጊው የሚጠየቀው በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 620-627 ስር ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ብቻ

ይሆናል፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሌላ ምሳሌ ብንወስድ አንድ ወንጀል አድራጊ አንድን ግለሰብ እየደበደበ፣ እየዛተ፣ እየቆራረጠ ቢገድለው ወንጀል ፈጻሚው በድርጊቱ ውስጥ በተለያየ ድንጋጌ ሊያስጠይቁ የሚችሉ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡ ሆኖም በአካል ጉዳት ማድረስ (አንቀጽ 556 /555)፣ በዛቻ (አንቀጽ 580፣ በመግደል ሙከራ (አንቀጽ 27(1)ና 540/539(1-ሀ)፣ በእጅ እልፊት ወንጀሎች ሊጠየቅ አይገባም፡፡ ምክንያቱም በሰው መግደል ወንጀል ውስጥ አካል ጉዳት ማድረስ፣ እጅ እልፊት፣ ዛቻ፣ ስድብ፣ መግደል ሙከራ ወንጀሎች ሊኖሩ የሚችሉና እነዚህ በጠቅላላው በሰው መግደል ወንጀል ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉና ብዙውን ጊዜ ሰው ለመግደል አስቦ ለተዘጋጀ ወንጀል አድራጊ የእጅ እልፊት፣ የአካል ጉዳት ማድረስ ስድብ ወይም የዛቻ ተግባሮችን መፈጸም የማይቀር የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ የስርቆት ወይም የውንብድና ወንጀል የሚፈጽም ወንጀል አድራጊም በአንቀጽ 604 መሰረት የግል ቤቶችን ወይም የተከለከሉ ቦታዎችን በመድፈር ወንጀል በአንቀጽ 665 ወይም በአንቀጽ 670/671 በተደራራቢ ወንጀል ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የስርቆት ወይም የውንብድና ወንጀል የሚፈጽም ወንጀል አድራጊ የግል ቤቶችን መድፈር የግድ ሊሆንበት ይችላል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ድርጊቶች የወንጀሉ ውጤት ከወንጀል አድራጊው ሀሳብ በላይ በሆነ ጊዜ ወንጀል አድራጊው ከአሳቡ በላይ ለሆነው ወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ‘ሀ’ በ ‘ለ’ ላይ የአካል ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በጩቤ ቢወጋውና ‘ለ’ ቢሞት ‘ሀ’ ተጠያቂ የሚሆነው አስቦ ከባድ አካል ጉዳት ማድረስ ሳይሆን ድርጊቱ ሞት ሊያመጣ እንደሚችል መገመት እየተገባው ባለማድረጉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 59 እና 543(1) መሰረት በቸልተኛነት ሰው መግደል ወንጀል ሊጠየቅ ይችላል፡፡ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶችና ዐቃብያነ ህግ መስሪያ ቤቶች በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት በወንጀል ህግ አንቀጽ 61/1/ መሰረት በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች የተደረጉት በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ በሆነ ጊዜ ለአንድ ድርጊት አንድ ቅጣት በሚለው መርህ መሰረት ሁሉንም ድርጊቶች የሚያጠቃልል አንድ ከባድ ድንጋጌ ካለ በሁሉም ድርጊቶች እንደማይቀጣ ይልቁንም በከባዱ ወንጀል ተጠቃለው እንደሚቀጣ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በአንድ የምርመራ መዝገብ ወንጀል አድራጊዎች በተከሰሱበት ከባድ ውንብድና ወንጀል ተከሳሾች በአንድ የግል ተበዳይ ላይ የውንብድና እና የአካል ጉዳት በማድረሳቸው ክሱ በከባድ ውንብድና ብቻ ተጠቃሎ መቅረብ ሲገባው በከባድ ውንብድና እና በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ክስ የቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል[37]፡፡ በሌላ መዝገብ አንድ ወንጀል አድራጊ በግል ተበዳይ ላይ ቀላል የአካል ጉዳት በማድረስ የግል ተበዳይን ንብረት

[37]የምዕራብ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ፣ የወ/መ/ቁ/ 04650 ዐቃቤ-ህግና ክንዲሁን አዳነ

የወሰደ መሆኑን የምርመራ መዝገቡ እያመለከተ በወንጀል አድራጊው ላይ የውንብድና እና የአካል ጉዳት በማድረስ 2 ተደራራቢ ክስ የቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡[38] በሌላ መዝገብ ወንጀል አድራጊው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ በመገልገል በፈጸመው የውንብድና ወንጀል ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 671ንና አንቀጽ 808 ን በመጥቀስ በከባድ ውንብድና እና በህገ ወጥ ጦር መሳሪያ መገልገል ወንጀል 2 ተደራራቢ ክስ ቢያቀርብም ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው ፍርድ ቤት ውንብድና በጦር መሳሪያ ሊፈጸም እንደሚችል በድንጋጌው ተመልክቷል በሚል በውንብድና ወንጀሉ ሊጠቃለል ይችላል በሚል ውሳኔ ሰጥቷል[39]፡፡ ይህ ውሳኔ የወንጀል ህግ አንቀጽ 61(1) ዓላማን ያላገናዘበ ውሳኔ ነው፡፡ ምክንያቱም ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ለውንብድና ወንጀል መፈጸሚያ የሚያገለግል ቢሆንም ስለውንብድና ወንጀል የተደነገጉት አንቀጾች ህገ ወጥ ጦር መሳሪያ መያዝን ወይም መገልገልን አጠቃሎ የያዘ አይደለም፡፡

ሌላው ህግ አውጭው ፍጹም ተዳራራቢ ያልሆኑ ተግባሮች በሚል ካስቀመጣቸው ውስጥ አንዱ በአንቀጽ 61(2) ስር የተመለከተው ነው፡፡ መመዘኛዎቹም፡-

> *“በህግ በተጠበቀ በዚያው በአንድ መብት ላይ፣ ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ ወንጀል ተግባሮች፣ በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን፣ እንደ አንድ ወንጀል ይቆጠራሉ፣ ወንጀል አድራጊው የሚቀጣው ለአንዱ ወንጀል ነው፣ እንዲሁም ወንጀል አድራጊው ደጋግሞ ወይም አከታትሎ ማድረጉ፣ ወይም ወንጀልን እንደ ልማድ ወይም ሙያው አድርጎ መያዙ ለአንድ ወንጀል ማቋቋሚያ ወይም ቅጣት ማክበጃ ካልሆነ በቀር ተደራራቢ ወንጀል አይባልም” የሚል ነው፡፡*

ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው በህግ ጥበቃ በተደረገለት በአንድ መብት ላይ ድርጊቶች ተደጋግመው ወይም ተከታትለው ቢፈጸሙ ወንጀል አድራጊው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ እስከ ፈጸማቸው ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደማይባሉ ነው፡፡ በድንጋጌው ውስጥ ከተካተቱት ቃሎች ውስጥ በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚለው የአንድን ሰው መብት የሚያመለክት ነውን? ወይስ መብቱ የተለያዩ ሰዎች ቢሆንም በአንድ ድንጋጌ ስር ጥበቃ የተደረገለትን መብት ነው? የሚለው የሚያከራክር ነው፡፡ በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የሚለውም አገላለጽ ወንጀል አድራጊዎች

---

[38]የዋግ ኽምራ ብሄረ ሰብ ዞን የወ/መ/ቁ 92/06፣ ዐቃቤ-ህግና ጎሸየ አማረ

ወንጀል ለመፈጸም የተነሳሱበትን የመጀመሪያ እቅድ ወይም አላማ የሚጠቁም ነውን? ድርጊቱን እየፈጸመ እያለ በዚያው ሰው መብት ላይ ወይም በሌላ ሰው ላይ ተመሳሳይ ወንጀል ለመፈጸም ቢያስብስ? በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ አይባልምን? የሚሉትን ሀሳቦች ከድንጋጌው መረዳት አይቻልም፡፡

የወንጀል ህግ በዋናነት የወንጀል አድራጊውን የሀሳብ ክፍል የመቅጣት ቀዳሚ አላማ እንዳለው ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ በአንቀጽ 61(2) ስር የተቀመጠውን ስንመለከትም አንድ ድርጊት የተፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ከሆነ ድርጊቶቹ ቢደጋገሙም ተግባሮቹ በተደራራቢነት እንደማያስቀጡና ወንጀል አድራጊው ደጋግሞ ለፈጸማቸው ተግባሮች እንደማይቀጣ የሚገልጽ መርህ ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ድርጊት በተፈጸመ ጊዜ ድርጊቱ የተፈጸመው በአዲስ ሀሳብ የተፈጸመው ነው አይደለም የሚለው በእጅጉ አስቸጋሪና አከራካሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ወንጀል አድራጊዎች አንድ ወንጀል ከፈጸሙ በኋላ ያንኑ ወንጀል በዚያው ሰው መብት ላይ ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ በድጋሚ ቢፈጽሙ በአዲስ ሀሳብ ነው አይደለም የሚለው በድርጊቱ ውስጥ ያሉትን ፍሬ ነገሮችና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በማየት እንደ የጉዳዮቹ አግባብ የሚወሰን ነው፡፡ በተለይም ድርጊት ፈጻሚው ድርጊቱን ለተወሰነ ጊዜ አቋርጦ እንደገና ቢፈጽምና ያቋረጠው ለቀናት? ለሳምንታት ቢሆን? ወንጀሉን የፈጸመው በሌላ ሰው መብት ወይም በሌላ አይነት መብት ላይ ቢሆን? ለተወሰነ ጊዜ የተቋረጠው ውጫዊ ባልሆነ ምክንያት ቢሆንስ? የሚሉትን ነጥቦች እያነሳን ስንጠይቅ ድንጋጌው አመላካች ነገር የለውም፡ የወንጀል አድራጊዎች የሀሳብ ሁኔታ /state of mind/ የሚታወቀው አንድን ወንጀል ደጋግመው ወይም አከታትለው ሲፈጽሙ አዲስ ሀሳብ ይዘው መሆን አለመሆኑን ለመረዳት ወንጀል አድራጊዎቹ ከሚናገሩት፣ ይዘው ከተነሱት እቅድ፣ ከሚጠቀሙት ዘዴ፣ በተደጋጋሚ በተፈጸሙት ድርጊቶች መካከል ያለውን የጊዜ ርዝመትና ሌሎች ፍሬ ነገሮችን በመያዝ የሚደረስበት ነው፡፡ አንድ ወንጀል የፈጸመ ሰው ድርጊቱን በተደጋጋሚ የፈጸመው በአዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ነው አይደለም የሚለውን ለመረዳት ጉዳዮቹን በምሳሌ ለመመልከት ያክል አንድ ወንጀል አድራጊ የቤት ውስጥ ጥቃት በተደጋጋሚ በአንዲት ሴት ላይ ቢፈጽም ወንጀል አድራጊው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ድርጊቱን ፈጽሞታል ለማለት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ አንድ ገንዘብ ያዥ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥራ ስትሰራ በቀን 5 ብር ለአንድ ዓመት ያክል ብትወስድ

የፈጸመችው ወንጀል ተከታታይ የእምነት ማጉደል ወንጀል ሲሆን በአንድ የንብረት መብት ላይ ገንዘብ ለማግኘት ካላት ፍላጎት በመነጨ ሀሳብ እና አከታትላ ያደረገችው ወንጀል ስለሆነ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676(2-ሀ) ስር የተመለከተው ተጠቅሶ እንደ አንድ ድርጊት ተቆጥሮ በአንድ ክስ ብቻ ተጠያቂ ትሆናለች፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ ሰው ለመግደል ያሰበ ሰው 5 ጊዜ ተኩሶ ቢስተው እና በ 6ኛው ቢገድለው በተደራራቢ ወንጀል አይጠየቅም፡፡ ነገር ግን ወንጀል አድራጊው ተኩሶ ስቶት ከሄደ ከሳምንት በኋላ ተመልሶ በመምጣት ቢገድለው በመግደል ሙከራና በሰው መግደል ወንጀል በተደራራቢ የሚጠየቅ ይሆናል፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ መኪና የሚያሽከረክር ግለሰብ ከሚነዳው መኪና ላይ የጫናቸው ጎማዎች በአግባቡ ባለመታሰራቸው አንደኛው ወድቆ አንድ ሰው ከመታ በኋላ ቀሪው ጎማም ሊወድቅ እንደሚችል የሚገመት ሆኖ እያለ አሽከርካሪው ቀሪውን ጎማ በአግባቡ ማሰር ሲገባው ይህን ባለማድረጉ ከተወሰነ ጉዞ በኋላ እንደገና ሁለተኛው ወድቆ ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ይጠየቃል፡፡ ምክንያቱም ሁለተኛው ወንጀል የተፈጸመው በአዲስ ቸልተኛነት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በሌላ ምሳሌ ‘ሀ’ ከአባቱ ኪስ በተከታታይ ቢሰርቅና አንድ ቀን አውቆበት ቢቆጣው ለተወሰነ ጊዜ አቋርጦ እንደገና ቢጀምር አዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ አለው ለማለት ይቻላል፡፡ በሌላ ምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ በርከት ያለ ህገ ወጥ ብር ገበያ ይዞ በመውጣት ከተለያዩ ሰዎች እህል በመግዛት ሀሰተኛ ገንዘቡ እንዲዘዋወር ቢያደርግ ድርጊቱ በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸመ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በሌላ ምሳሌ በአንድ የገጠር ቀበሌ ውስጥ አንድ የቀበሌ አመራር ለስራ አጥ ወጣቶች የገጠር መሬት ለመስጠት በማሰብ በአንድ ቀን ውስጥ ከተለያዩ ወጣቶች 900 ብር አምጡና መሬት ልስጣችሁ በማለት ገንዘብ ቢቀበል ወንጀሉን የፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

የወንጀል አድራጊዎችን የሀሳብ ሁኔታ ፈልጎ በማግኘት አንድ ድርጊት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸመ ነው አይደለም የሚለው እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ጉዳዩን ተደራራረቢ ይሆናል አይሆንም በሚለው ዙሪያ በባለሙያዎች ዘንድ ሰፊ ልዩነትና ክርክር ሲደረግ ይታያል፡፡ በአንድ ወቅት በአማራ ክልል በተለያዩ ከተማ አስተዳደሮች በመሬት ማስተላለፍ የስራ ሂደት ውስጥ

ይሰሩ የነበሩ የስራ ሀላፊዎችና ባለሙያዎች ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ለተለያዩ ግለሰቦች በተለያየ ጊዜ መሬት አላግባብ አስተላልፈዋል በሚል ምርመራ ተጣርቶባቸው ክስ ለማቅረብ ድርጊቱ የተፈጸመው በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ነው አይደለም በሚል በጸረ ሙስና ዐቃብያነ ህጎች መካከል ሰፊ ክርክርና ልዩነት ስለነበር በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ድርጊቱ በአዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ የተፈጸመ ነው በሚል ተደራራቢ ክሶች የቀረቡ ሲሆን ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሌሎች መዝገቦች ድርጊቱ የተፈጸመው በአንድ ወንጀል በማድረግ ሀሳብ ነው በሚል ወንጀሉ ተደራራቢ አይሆንም በሚል እንደ አንድ ድርጊት ተቆጥሮ አንድ ክስ እንደቀረበ ባለሙያዎች ይገልጻሉ[40]፡፡

ሌላው በአንቀጽ 61(2) ሁለተኛ ፓራግራፍ ስር የተገለጸው የድርጊቶች መደጋገም ተደራራቢ ወንጀሎች መሆናቸው ይቀርና የድርጊቱ መደጋገም በራሱ አንድን ወንጀል የሚያቋቁም ወይም የቅጣት ማክበጃ የሚሆንበት አጋጣሚ እንዳለ በድንጋጌው ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ድርጊቶች ከአንድ ወንጀል ከመፈጸም ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት የሚመነጩ ሲሆን በመጀመሪያው ፓራግራፍ ከተመለከተው የተለየ የሚያደርጋቸው ወንጀል አድራጊው ድርጊቶቹን መደጋገሙ በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ለተደነገጉ የተለያዩ አንቀጾች ማቋቋሚያ ምክንያት መሆናቸው ነው፡፡ የድርጊቶች መደጋገም የድንጋጌዎቹ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሆነባቸው ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በወንጀል ህጉ ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን ለምሳሌ በአንቀጽ 471 አደገኛ የሆነ ስራ ፈትነት፣ አንቀጽ 634 የሌላውን ሰው የዝሙት ድርጊት የዘወትር መጠቀሚያ ማድረግ፣ አንቀጽ 635 ሴቶችንና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት አዳሪነት በማቃጠር መነገድ፣ በአንቀጽ 477 አደገኛ ቦዘኔነት፣ አንቀጽ 478 የክፉ አድራጊዎች ማህበር፣ አንቀጽ 535 በህክምና ጤና አጠባበቅ ሙያ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መስራት፤ አንቀጽ 354 ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት የተደረገ ህገ ወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ መስራትን የዘወትር የሞያ ስራው ያደረገ ሰው የመሳሰሉት ድንጋጌዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በመርህ ደረጃ በአንቀጽ 61(2) ላይ የተመለከትናቸው ድርጊቶች በተደራራቢነት እንደማያስቀጡ የተደነገገ ቢሆንም ድርጊቱ በአዲስ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ከሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 62 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙ ጊዜ ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀል

[40]በአብክመ የጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ ከደብረ ብርሀን ቋሚ ምድብ ችሎት ዓቃቢያነ ህግ ጋር የተደረገ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 4/2008

ተጠያቂ ይሆናል[41]:: በአንቀጽ 62 ስር የተቀመጠው መስፈርት *"ቀድሞ አድርጎት ከነበረው ወንጀል ጋር ተመሳሳይ የሆነ፣ በአዲስ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ በሌላ ሰው ወይም ቀድሞ ፈጽሞት በነበረው ሰው ላይ ቢሆንም፣ ወይም በህግ በተጠበቀ በዚያው መብት ላይ ቢሆንም እንኳ አዲስ ወንጀል ስለሆነ በ 184 መሰረት ተደራራቢ ይሆንበታል"::*

በወንጀል ህጉ ተደራራቢ ያልሆኑ ወንጀሎች ከሚመጡበት ሌላው ምክንያት በአንቀጽ 61(3) ስር የተመለከተው ነው። በዚህ ድንጋጌ ስር ድርጊቶቹ ለዋናው ወንጀል ቅጥያ /Ancillary (subordinate) በሆኑ ጊዜ ወንጀል አድራጊው ለሁሉም ድርጊቶች ተጠያቂ አይሆንም። ይልቁንም ወንጀል አድራጊው ተጠያቂ የሚሆነው መጀመሪያ ለመፈጸም አቅዶ ለተነሳው ወንጀልና ለዋናው ወንጀል ብቻ ይሆናል። በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጠው መመዘኛ፡-

> *"አድራጊው የተወሰነ ወንጀል ለማድረግ ሀሳብ አለው ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ፤በተለይም የማይገባውን ብልጽግና ለማግነት በማሰብ በንብረት ላይ ወንጀል አድርጎ እንደሆነ፤ ወይም የሀሰት ገንዘብ ሰርቶአ ንደሆነ፤ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ፤ ወይም ሀሰተኛ ገንዘብ ሰርቶ እንደሆነ፤ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ፤ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ ሰርቶ እንደሆነ ወይም ተጠቅሞበት እንደሆነ፤ የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሲል፤ መሰረታዊ ከሆነው ወንጀል በኋላ አከታትሎ የፈጸመው ከቀድሞው አሳቡና ሊደርስበት ካሰበው ግቡ ጋር የተያዘ ሆኖ በዋናው ወንጀል ይጠቃለል" የሚል ነው::*

ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው አንድ ወንጀል አድራጊ አንድ ነጠላ የሆነ ውጤት ለማምጣት በማሰብ ብዙ ህገ ወጥ ድርጊቶችን የፈጸመ እንደሆነ ወንጀሎቹ በጣም የሚቀራረቡ ከሆነ የጥፋተኝነት ሀሳብ ያለው በዋናው ወንጀል ላይ እንደሆነ ስለሚወሰድ ሌሎቹ ድርጊቶቹ የዋናው ወንጀል ቅጥያ በመሆን ስለሚወሰዱ ስለእነዚህ ድርጊቶች በተደራራቢነት ተጠያቂ አይሆንም ማለት ነው። ይህ ማለት መጀመሪያ የተፈጸመው ወንጀል ፍሬ ያፈራ ዘንድ የግድ የሚቀጥለው ወንጀል መፈጸም የሚኖርበት ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ወንጀል አድራጊ የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ሀሰተኛ ገንዘብ አዘጋጅቶ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅቶ ይህንኑ ገንዘብ ገበያ

[41]ይህን ነጥብ በሚመለከት በአንድ ወቅት በአማራ ክልል ጸረ ሙስና ኮሚሽን ውስጥ በሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች መካከል ቃሉን በመረዳት ረገድ ልዩነት ስለነበር በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ሁለት ዓይነት ክሶች የቀረቡ ሲሆን በአንደኛው መዝገብ ላይ በወንጀሎቹ መካከል ያለው ጊዜ የተራራቀ ስለሆነ ተደራራቢ ሊሆን አይገባም በሚል በተለያዩ መዝገቦች ክስ የቀረበ ሲሆን በሌላ በኩል በድርጊቶቹ መካከል ያለው ጊዜ ሩቅ ቢሆንም በሁለቱ ድርጊቶች መካከል ይርጋ እስካላገደው ድረስ ተደራራቢነቱን አያሳጣውም በሚል በተደራራቢነት ክስ እንደቀረበ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

ውስጥ እንዲዘዋወር ቢያደርግ ወይም ሀሰተኛ ሰነዱን ቢገለገልበት ወንጀል አድራጊው የሚጠየቀው ለዋናው ወንጀል ለህገ ወጥ ብር ማዘጋጀቱ ወይም ለሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ እንጂ ህገ ወጥ ገንዘብ ለማዘዋወሩ ወይም በሀሰተኛ ሰነዱ በመገልገሉ ተጠያቂ አይሆንም። ምክንያቱም ማዘዋወሩ የማዘጋጀት ወንጀሉ ቅጥያ ወንጀል ስለሆነ ማለት ነው። ነገር ግን በሀሰተኛ ሰነዱ በመገልገል የማታለል ወንጀል ተፈጽሞ ከሆነ ለሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 378 ወይም በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 መሰረትና በወንጀል ህግ አንቀጽ 699 መሰረት በማዘጋጀትና በማታለል ወንጀል 2 ተደራራቢ ክስ ይቀርብበታል። በወንጀል ህጉ አንቀጽ 369 መሰረት እንደተመለከተው ሀሰተኛ ሰነድ የተገለገለ ሰው የሚጠየቀው በመገልገሉ ብቻ ነው። ሀሰተኛ ሰነዱን እስካላዘጋጀው ወይም በማዘጋጀቱ ውስጥ እስካልተሳተፈ ድረስ። ለምሳሌ አቶ ደፋሩ በሐሰተኛ የምስክር ወረቀት በመገልገል አንድን የመንግሥት መሥሪያ ቤት አታሎ ከተቀጠረ በኋላ የሶስት ወር ደመወዝ እንደተቀበለ ቢደርስበት የሚከሰሰውና የሚቀጣው በሐሰተኛ የትምህርት ምስክር ወረቀት በመገልገሉ በወንጀል ሕግ ቁጥር 369 አታሎ የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፈለው በማድረጉ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 696 መሠረት ነው። በተጨማሪም በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 388 ስር እንደተገለጸው ማንም ሰው ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት፣ ሀሰተኛ የምስክርነት ማስረጃ ወይም እርሱን የማይመለከተውን ወይም እንዲገለገልበት ያልታሰበውን ትክክለኛ የምስክር ወረቀት አግኝቶ በዚሁ አስቦ በመጠቀም ተጨማሪ ወንጀል ለመፈጸም የተገለገለበት እንደሆነ በተለይም እምነት ማጉደል ወንጀል ወይም ማታለል ወንጀል ሆኖ ወንጀሉ ቢያንስ ተሞክሮ ከሆነ በአንቀጽ 66 መሰረት በተደራራቢነት እንደሚጠየቅ የሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገልን በሚመለከት በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት ሀሰተኛ ሰነድ መገልገልና ማዘጋጀት ወንጀል በአንድ ድንጋጌ ይጠቃለል የሚለው ነጥብ በባለሙያዎች ዘንድ በስፋት ሲያከራክር ይታያል። አንዳንድ ባለሙያዎች ጽንሰ ሀሳቡን በአግባቡ ባለመረዳት በሀሰተኛ ሰነድ ሲገለገል የተገኘን ወንጀል አድራጊ በሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና በመገልገል በ 2 ተደራራቢ ክስ የሚያቀርቡ እንደነበሩ ባለሙያዎች ይገልጻሉ[42]። አንዳንድ ባለሙያዎች ከላይ ከተገለጸው በተለየ ሁኔታ ሀሰተኛ ሰነዱን ያዘጋጀውና የተገለገለው አንድ ወንጀል አድራጊ በሆነ ጊዜ መገልገሉ የማዘጋጀቱ ቅጥያ ነው በሚል በማዘጋጀት ብቻ ክስ እንደሚያቀርቡ ይገለጻል[43]።

[42]በአብክመ የጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ የደብረብርሀን ቋሚ ችሎት ከሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች ጋር የተደረገ ውይይት፣ ሚያዚያ 21/2008 ዓ.ም
[43] ዝኒ ከማሁ

## 3. በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ የቅጣት አጣጣል መርሆዎችና ተግባራዊ አፈጻጸሙ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች

ከተደራራቢ ወንጀሎች ጋር በተገናኘ አቢይ ትኩረት ከሚስቡ ጉዳዮች አንዱና በፍርድ ቤቶችም ችግር ሲፈጥር የሚታየው በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ የቅጣት አጣጣል ስልት ነው፡፡ በብዙ ሀገራት የወንጀል ህግ ውስጥ የእኛንም ጨምሮ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተብለው ከሚመደቡት ውስጥ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚጠቀሱ ናቸው[44]፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎች ልዩ የቅጣት ማክበጃ ሆነው ቢደነገጉም ምንጊዜም ቢሆን ቅጣት ሲጣል የተመጣጣኝነት መርህንና የሚጣለው ቅጣት የሚፈጸም መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት እንዴት እንደሚጣል የሚጠቁሙ መርሆዎች ከአንቀጽ 183-188 ባሉት ድንጋጌዎች ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎች ስንመለከት ቅጣት ተመጣጣኝ መሆኑን ለማመልከት የተቀመጡ ድንጋጌዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡

በብዙ ሀገራት የወንጀል ህግ ውስጥ የእኛንም ጨምሮ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል ስራ ላይ ከዋሉ ዘዴዎች ውስጥ የመደመር /totality/ comulation rule/ እና የማጠቃለል /absorbtion rule/ የሚባሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### ሀ. የመደመር /totality/ የቅጣት አጣጣል ዘዴ

የመደመር ቅጣት አጣጣል ዘዴ በብዙ ሀገሮች የወንጀል ህግ ውስጥ የሚገኝና በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል ዋነኛው ዘዴ ነው[45]፡፡ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል የመደመር መርህ አማራጭ የሆነበት ምክንያት በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ትክክለኛና ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ለመጣል ያስችላል ከሚል እምነት ነው፡፡ ምክንያቱም ወንጀል አድራጊዎች ለፈጸሟቸው ሁሉም ወንጀሎች ቅጣት ተጥሎ ሁሉም ቅጣቶች ስለሚደመሩ የወንጀል አድራጊውን የአደገኛነት መጠን በሚያሳይ መልኩ ስለሚወሰን የተመጣጣኝነት መርህን ስለሚያስጠብቅ ነው፡፡ በእርግጥ በተደራራቢ ወንጀሎች ጉዳይ ለነጠላ ወንጀሎቹ የተቀመጠውን ቅጣት በመደመር ብቻ ሁል ጊዜ ተመጣጣኝና ትክክለኛ ቅጣት ለመጣል አይቻልም፡፡

---

[44]በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 85 ስር እንደተመለከተው ተደራራቢ ወንጀል ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተብለው ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡
[45]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7

የመደመር /totality/ የቅጣት አጣጣል ዘዴ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 184(1-ለ) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን መርሁ በብዙ ሀገሮች የወንጀል ህግ ውስጥ ተካቶ የሚገኝና በስፋት የሚሰራበት ነው፡፡ የመደመር ዘዴ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገበት ምክንያት በተደራራቢ ወንጀሎች ከደረሰው ጉዳት እና ከወንጀል አድራጊው የአደገኛነት ባህሪ በመነሳት በወንጀል አድራጊዎች ላይ ትክክለኛና ተመጣጣኝ ቅጣት ለመጣል ነው፡፡ ስለሆነም የመደመር ዘዴ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት አጣጣልን በሚመለከት ዋነኛው መርህ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በመደመር ዘዴ መሰረት ለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት የሚሰላው ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ እነዚህን መነሻዎች በመደመር ድምሩ የሚያርፍበትን ውጤት በመያዝ ማክበጃና ማቅለያ በቅደም ተከተል በመያዝ የሚወሰን ነው፡፡ በመደመር የቅጣት አጣጣል ዘዴ ቅጣት የሚጣለው ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ ሁሉንም በመደመር የሚሰላ ነው፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች ተደምረው የሚገኘው አጠቃላይ ውጤት ወንጀል አድራጊው ላይ የሚወሰን ሲሆን በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ ወንጀል አድራጊው ላይ የሚጣለው ቅጣት ተደራራቢ ወንጀሎቹ ተደምረው የሚገኘው የመጨረሻ ውጤት ሳይሆን በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል የተቀመጠው የጠቅላላ የጽኑ ወይም የቀላል እስራት ጣሪያ ሳያልፍ መሆኑ ተደንግጎ ይገኛል[46]፡፡ ይህ ማለት ተደራራቢ ወንጀሎቹ ተደምረው የሚገኘው ውጤት በጠቅላላ የወንጀል ህጉ ክፍል ውስጥ ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ ካለፈ ትርፉን ቁጥር ውድቅ በማድረግ እንዳይፈጸም ይደረጋል፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች ተደምረው የሚገኘው ውጤት በወንጀል አድራጊው ላይ የሚጣል ሲሆን በመደመር ቅጣት የሚጣለው ቅጣት ከወንጀል አድራጊው እድሜ በላይ ሊሆን የሚችልና የማይፈጸም ቅጣት እንደሚሆን የሚታወቅ ቢሆንም ቅጣት በአንድ ሀገር ውስጥ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥና ቅጣት ለሌሎች አስተምህሪ መሆኑን ለማሳየት የሚጣል ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀል ህግ በአንቀጽ 184 /1-ለ/ ስር በተገለጸው መሰረት ከሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡና ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶችን የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈጸመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም እንደሚደመር ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የሚገኘው ውጤት በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተቀመጠው ጣሪያ ሊበልጥ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በጽኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ለመደመር እንዲያመች የሁለት ዓመት

---

[46]ለምሳሌ የደቡብ አፍሪካን የወንጀል ህግ ስንመለከት በወንጀል ህጉ የተቀመጠ ጣሪያ የለም፡፡ ተዳራራቢ ወንጀሎቹ ተደምረው የሚገኘው ውጤት በወንጀል አድራጊው ላይ ይወሰናል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 106ና 108 ላይ እንደተቀመጠው የቀላል እስራት ጣሪያ 3 ዓመት ሲሆን የጽኑ እስራት ደግሞ 25 ዓመት ነው፡፡

ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚቆጠር ተቀምጧል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት አወሳሰን ቁጥር 2 መመሪያ መሰረትም ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ ከተባለ ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ እነዚህን በመደመር የድምሩ ውጤት የሚያመለክተውን ቁጥር በመያዝ ዝቅተኛ እርከኑ እንደሚመረጥ ይጠቁማል፡፡ በመቀጠልም የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ እርከኑን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ ቅጣት እንዲሚወሰን ተመልክቷል[47]፡፡ በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ መሰረት ጽኑ እስራት ከ 25 ዓመት እንደማይበልጥ የተደነገገ ሲሆን ቀላል እስራት ደግሞ በመርህ ደረጃ ከ 3 ዓመት በልዩ የወንጀል ህጉ ክፍል ላይ በተመለከተ ጊዜ ከ 5 ዓመት እንደማይበልጥ ተደንግጓል[48]፡፡ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ በሁሉም የተደራራቢ ወንጀሎች ላይ የቅጣት መደመር አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ተደምሮ የሚጣለው ቅጣት ምናልባትም አንድ ሰው ወይም የሚጣልበት ሰው በህይወት ከሚኖረው እድሜ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከሞተ በኋላ ያለው ቅጣት የማይፈጸም ቅጣት ስለሚሆን በወንጀል ህጉ ከተቀመጠው ጣሪያ ውጭ ይሆናል እንደ ማለት ነው፡፡ በጽኑ እስራት ጊዜም ሁሉም ይደመሩ ከተባለ የሚጣለው ቅጣት ከ 25 ዓመት በላይ ይሆናል፡፡ ከቅጣት መደመር ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች ጋር በተደራራቢነት የሚመጡ ከሆነ ቅጣት እንዴት ሊወሰን ይችላል የሚለው ነው፡፡ በወንጀል ህግ ከአንቀጽ 776-865 ያሉት ድንጋጌዎች የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች ሲሆኑ በእነዚህ ተግባራት ጥፋተኛ የተባሉ ወንጀል አድራጊዎች የሚጣልባቸው ቅጣት በገንዘብ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት በመሆኑ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች ጋር ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ለመደመር ያመች ዘንድ በማረፊያ ቤት የሚያስቀጣ የደንብ መተላለፍ ወንጀል እንዴት ወደ ጽኑ እስራት ወይም ቀላል እስራት እንደሚቀየር በህጉ አልተቀመጠም፡፡ ቅጣቱ በእስራት ሆኖ በማረፊያ ቤት እንዲፈጸም ፍርድ ቤቱ ቢወሰን በሀገራችን ማረፊያ ቤት ባለመኖሩ ለማስፈጸም ችግር መፍጠሩ አይቀርም፡፡ በተግባር ያለውን

---

[47]የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅታት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 22(1-ሀ)
[48]የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 108ና 106

አሰራር ስንመለከትም ፍርድ ቤቶቻችን ይህን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል በአማራጭ የተቀመጠውን የገንዘብ መቀጮ ሲቀጡ ማየት የተለመደ ነው[49]፡፡

### ለ. የማጠቃለል (absorbtion) የቅጣት አጣጣል ዘዴ

በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመጣል በብዙ ሀገራት የወንጀል ህጎች ውስጥ ተካቶ ከሚገኙ መርሆዎች ውስጥ አንዱ የማጠቃለል ዘዴ ነው፡፡ ይህ መርህ ተግባራዊ የሚሆነው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎች በተደራራቢነት ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣው ወንጀል ይወሰድና ሌሎቹ በከባዱ ወንጀል እንዲጠቃለሉ በማድረግ ቅጣት የሚጣልበት ዘዴ ነው፡፡ ለምሳሌ ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት እንደ ሞት ወይም እድሜ ልክ የሚያስቀጡ ቢሆን ሌሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡት ወንጀሎች በሞት ወይም በእድሜ ልክ በሚያስቀጣው ወንጀል እንዲጠቃለሉ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት የሚያሰቀጡ ሆነው በተገኙ ጊዜ በንጽጽር ዝቅተኛ ቅጣት የሚያስቀጡት ወንጀሎች በከባድ ጽኑ እስራት ወይም ከፍ ባለ ቀላል እስራት በሚስያቀጡ ወንጀሎች እንዲጠቃለሉ ይደረጋል፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት በሚጣልበት ጊዜ በከባዱ ወንጀል እንዲጠቃለል የሚደረግበት ዓላማ  በሞት ወይም በእድሜ ልክ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከሌሎች በሞት ወይም በእድሜ ልክ ወይም በእስራት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች ጋር በተደራራቢነት ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በተጨማሪ በሞት፣ በእድሜ ልክ ወይም በእስራት የሚያስቀጣ ቅጣት ቢጣል ቅጣቱ የማይፈጸም ስለሚሆን ቅጣት መጣሉ ትርጉም አልባ ስለሚሆን ነው፡፡ በሌላ በኩል የማጠቃለል የቅጣት አጣጣል ዘዴን ተግባራዊ የምናደርግበት አጋጣሚ ተደራራቢ ወንጀሎቹ የተፈጸሙት በጣምራ የወንጀል ድርጊት ወይም ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኛነት ሲሆን ነው፡፡ በጣምራ ወንጀል ተግባር ወይም በቸልተኛነት ተደራራቢ ወንጀሎችን የፈጸመ ወንጀል አድራጊ ባህሪውን ስንመለከት ግዙፋዊ ወንጀል ወይም ወንጀሎችን አስቦ ከፈጸመ ወንጀል አድራጊ ጋር ሲነጻጸር አደገኛ የሚባል አይነት ስላልሆነ የቅጣት ዓላማ ብቀላ ሳይሆን ማስተማር መሆኑን በተግባር ለማሳየት በጣምራ ወንጀል ወይም ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኛነት በሆነ ጊዜ ቅጣት የሚጣለው ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣው ወንጀል ይወሰድና ሌሎቹ

---

[49]በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በሰሜን ሸዋ ዞን ፍትህ መመሪያ በወንጀል የስራ ሂደት ከሚሰሩ ባለሙያዎች ጋር የተደረገ የጋራ ውይይት፣ ሚያዚያ 2/2008 ዓ.ም

ተደራራቢ ወንጀሎች እንደ ቅጣት ማክበጃ ተደርገው ይወሰዳሉ[50]፡፡ የማጠቃለል መርህ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 184(1-ሀ) ስር የተደነገገ ሲሆን ወንጀል አድራጊው *"ነጻነትን ወይም ህይወትን በማሳጣት ከሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም እድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ 108 ና 106/ ሲወሰን ---ይህ ውሳኔ ስለሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ሁሉ አጠቃሎ /ደርቦ/ ይይዛል"* በማለት ያስቀምጣል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184/1-ሀ/ ስር እንደተመለከተው ነፃነትን ወይም ህይወትን በሚያሳጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም የእድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ 106 እና 108/ ሲወሰን ይህ ውሣኔ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ /ደርቦ/ እንደሚይዝ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ በሞት ወይም በእድሜ ልክ ወይም ቅጣቱ ጽኑ እስራት ከሆነ የመጨረሻውን ጣሪያ 25 ዓመት የሚያስቀጣ ሲሆን ሌሎቹ ቅጣቶች በሞት ወይም በእድሜ ልክ ወይም በ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲጠቃለሉ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ በማጠቃለል መርህ ውስጥ አልፎ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ከያዘ በኂላ በስተመጨረሻ ከባዱን ቅጣት ያልወሰነ እንደሆነ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን በአንቀጽ 184(1-ለ) መሰረት እንደሚያሳድግ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) ሁለተኛ ፓራግራፍ ስር ተደንግጓል፡፡ ይህም የሚያሳየው ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲጥል የእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ቅጣት ለየብቻው ሲሰላ ከላይ በንዑስ ቁጥር 1/ሀ/ ፖራግራፍ 1 ስር እንደተቀመጠው የሞት ፍርድ፣ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛውን ቅጣት አለመቅጣቱን ካረጋገጠ ስሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን ማሳደግ እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት መነሻ ቅጣት መያዝ እና የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት የተለያዩ እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም በድንጋጌው ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ከቅጣት ዓይነቶቹ አንዱን የወሰነ እንደሆነ የሚለው የሚያመለክተው መነሻውን የወሰነ እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ አንድ ወንጀል አድራጊ ሁለትና ከዚያ በላይ

[50] የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 187(1) እና (2-ለ) ስር የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያሳዩት የማጠቃለል መርህን ነው፡፡

ወንጀል ሲፈፅም የአደገኛነት መጠኑ ስለሚለያይ እና መቀጣትም ያለበት በዚሁ የአደገኛነቱ ልክ በመሆኑ ነው፡፡

ከማጠቀለል መርህን ጋር በተያያዘ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ያለውን አሰራር ስንመለከት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) በሚያዘው መሰረት ዝቅተኛ ቅጣት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከባድ ቅጣት በሚያስቀጡት ወንጀሎች አልፎ አልፎ በማጠቃለል መርህ ቅጣት እንደማይወሰን ባለሙያዎች ይገልጻሉ[51]፡፡ እንደ ምክንያት የሚቀርበው በወንጀል ህጉ ላይ የተመለከቱትን መርሆዎች ባለሙያዎች በአግባቡ ባለመረዳት እንደሆነ ነው የሚል ነው[52]፡፡ ለምሳሌ ያክል በአንድ መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ወስደን ብንመለከት ወንጀል አድራጊው በ 2 ከባድ ሰው መግደልና በ 3 ተራ ሰው መግደል ሙከራ ወንጀል በድምሩ በ 5 ተደራራቢ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት የወንጀል አድራጊውን ባህሪ በመመልከት መነሻ ቅጣት የእድሜ ልክ መነሻ ቅጣት ከያዘ በኋላ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) በሚያዘው መሰረት ሌሎቹ ወንጀሎች በእድሜ ልክ እስራት በሚያስቀጣው ወንጀል ይጠቃለሉ በማለት ካጠቃለለ በኋላ 3 የቅጣት ማቅለያ በመቀበል በቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ለ 1 ቅጣት ማቅለያ 3 እርከን በመውረድ በድምሩ 9 እርከን በመውረድ ወንጀል አድራጊው በ 12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል[53]፡፡ይህን ውሳኔ ስንመለከት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184(1-ሀ) 2ተኛ ፓራግራፍ ስር የተመለከተውን መርህ ያላገናዘበ ነው፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ በስተመጨረሻ የጣለው ቅጣት ቀድሞ መነሻ የያዘውን የእድሜ ልክ ቅጣት ባለመሆኑ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን ማክበድ እንደሚገባ ህጉ በግልጽ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ማቅለያ በመጠቀም ቅጣቱ ወርዶ 12 ዓመት ላይ ሲደርስ በተመሳሳይ የቅጣት ማቅለያዎች ለሌሎቹም በእድሜ ልክ ያስቀጡ ለነበሩት ተደራራቢ ወንጀሎች በትይዩ ቅጣት ማቅለያው ስለሚሰራ በውስጠ ታዋቂነት ለሁሉም ወንጀሎች ቅጣቱ ቀሎ 12 ዓመት እንደደረሰ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የመጨረሻውን ቅጣት ሲወስን እስከ 25 ዓመት ጸኑ እስራት ድረስ ለመቅጣት እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

---

[51]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 29 የተገለጸው
[52] ዝኒ ከማሁ
[53]የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት የወ/መ/ቁ/ 0236951 በዐቃቤ ህግና በጌትነት ሰረቀ መካከል የተደረገ ክርክር

ሌላው የማጠቃለል መርህ የተመለከተው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 187(2-ለ) ሁለቱም በቸልተኛነት የተፈጸሙ ጣምራ ወንጀሎች ሆነው ግዙፋዊ ውጤት ያስከተሉ እንደሆነ ነው፡፡ የቅጣት አወሳሰን መመሪያው በአንቀጽ 22(1-ለ) ለአፈጻጸም ይረዳ ዘንድ በአንቀጽ 187/2-ለ/ መሰረት የሚኖር የወንጀል መደራረብ ባጋጠመ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንጀል ከመነሻው በ ሁለት እርከን እንዲያድግ ይደረጋል በሚል አስቀምጧል፡፡ ይህ ማለት በጣምራ ወንጀሎች ከተፈጸሙት ወይም ተደራርበው ከተጣሱት የህግ ድንጋጌዎች ውስጥ ለከፍተኛው መነሻ ቅጣት በማስቀመጥ ሌሎቹን እያንዳንዳቸውን እንደ ቅጣት ማክበጃ በመጠቀም ለእያንዳንዳቸው ከመነሻ ቅጣቱ በሁለት እርከን ማሳደግ ይገባል የሚል ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በሚያሽከረክረው መኪና አንድ ሰው ቢገድል እና ሁለት ሰው ላይ የአካል ጉዳት ቢያደርስ በአንድ ድርጊት 3 ጣምራ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡ ይሄውም በቸልተኝነት ሰው መግደል እና በቸልተኛነት በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል (አንቀጽ 60/ለ/ ሁለተኛ ፓራግራፍ) ቅጣቱ ሲሰላም በቸልተኛነት ለተፈጸመው ለሰው መግደሉ መነሻ ቅጣት በመስጠት ሁለቱን የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀሎች ለእያንዳንዳቸው በ 2 እርከን በማሳደግ ከመነሻ ቅጣቱ በ 4 እርከን በማሳደግ ቅጣት ይጣላል ማለት ነው፡፡ በአማራ ክልል በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከት ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች በቸልተኛነት የተፈጸሙ መሆናቸው ቢታወቅም ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 187(2-ለ) መሰረት ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣውን በመውሰድ ሌሎቹን እንደ ቅጣት ማክበጃ በማድረግ እንደማይሰራና ቅጣት የሚጣለው በመደመር እንደሆነ ባለሙያዎች ይገልጻሉ[54]፡፡ በአንድ መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት ዐቃቤ ህግ ባቀረበው በቸልተኛነት ሰው መግደልና በ 2 ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ 3 ተደራራቢ ክስ ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ በሁሉም ክሶች ጥፋተኛ ካለ በኂላ ለእያንዳንዱ ወንጀል ደረጃና እርከን በማውጣት መነሻ ከያዘ በኂላ ሁሉንም ወንጀሎች በመደመር ቅጣት ወስኗል[55]፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የወንጀሉን ደረጃና እርከን በማሻሻል በተመሳሳይ የመደመር ስሌትን በመከተል ሁሉንም ተደራራቢ ወንጀሎች ደምሮ ቅጣት እንደወሰነ መዝገቡ ያመለክታል[56]፡፡

[54]ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 29
[55]የሰሜን ሽዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት/የወ/መ/ቁ. 0237320 የጠ/ፍ/ቤቱ 02-17007 ክሱ 2 በቸልተኛነት ሰው መግደልና አንቀጽ 543(3) በቸልተኛት በአካል ላይ ጉዳት አንቀጽ 559(2) ማድረስ ጥፋተኛ ተብለው ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲጥል ለሁለቱም መነሻ ቅታት በመያዝ በመደመር እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡
[56]የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት የደብረ ብርሀን ቋሚ ችሎት የወ/መ/ዝ.ቁ. 16648 በዓቃቤ ህግና በጌትነት አምታቴ መካከል የተደረገ ክርክር

## 4. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

ተደራራቢ ወንጀሎች በባህሪያቸው ውስብስብ ስለሆኑና በፍሬ ነገር ላይ የተመሰረቱ ስለሆነ አንድን ድርጊት ተደራራቢ ነው አይደለም የሚለውን እንዲሁም ተደራራቢ የሆኑትን ተደራራቢ ካልሆኑት ወንጀሎች ለመለየትና ክስ አቅርቦ በፍርድ ቤት ውሳኔ ለመስጠት ቀላል ስራ አይደለም፡፡ በተለይም አንዳንድ ድርጊቶች ከላይ ሲታዩ ተደራራቢ የሚመስሉ ነገር ግን በጥልቀት ሲመረመሩ በአንድ ድንጋጌ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ወይም ተደጋግመው ስለተፈጸሙ ብቻ ተደራራቢ ሊባሉ እንደማይገባ ህግ አውጭው ያስቀመጣቸው አሉ፡ ተደራራቢ ያልሆኑ የወንጀል ተግባሮችን በህግ አውጭው ከተቀመጠው ውጭ አላግባብ ተደራራቢ አድርጎ በመፈረጅ ወንጀል አድራጊው አላግባብ ከፍተኛ ቅጣት እንዳይጣልበት ባለሙያዎች ጽንሰ ሀሳቡን በአግባቡ በመረዳትና ፍሬ ነገሮችን ከወንጀል ህጉ ጋር በማገናዘብ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲወሰን የሚጣለው ቅጣት ከደረሰው ጉዳት አንጻር ተመጣጣኝ እንዲሆን በማሰብ የመደመርና የማጠቃለል የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ተግባራዊ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በተለይም እንደ ሞት፣ እድሜ ልክ ወይም በመጨረሻው ጽኑ እስራት ወይም ቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከሌሎች ጋር ተደራርበው በመጡ ጊዜ ዝቅተኛ የሚያስቀጡት ወንጀሎች ከባድ ቅጣት በሚያስቀጡት ወንጀሎች እንዲጠቃለሉ የሚደረግበት ዘዴ ተቀምጧል፡፡ እንዲሁም ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኛነት ወይም በጣምራ በሆነ ጊዜ ወንጀል አድራጊው አደገኛ የሚባል ባለመሆኑና ድርጊቱም አንድ ነጠላ ድርጊት በመሆኑ ቅጣቱ ሲጣል ከባዱ ወንጀል ከተመረጠ በኂላ ሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደ ቅጣት ማክበጃ ሊወሰዱ እንደሚገባም በወንጀል ህጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ የተደራራቢ ወንጀሎች ጽንሰ ሀሳብ በባለሙያዎች ዘንድ በአግባቡ ያላደገ በመሆኑ በፍርድ ቤቶችና በዐቃቢያነ ህግ መስሪያ ቤቶች በተግባር ጉድለቶች ይስተዋላሉ፡፡ ይሄውም በአንዳንድ ውስብስብ ጉዳዮች ተደራራቢ መሆን የሚገባቸውን ወንጀሎች በአንድ ድንጋጌ ይሸፈናሉ በሚል ክስ እንደሚቀርብና ቅጣት እንደሚወሰን መዛግብቶች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል ህግ አውጭው አንዳንድ ጉዳዮች ከላይ ሲታዩ ተደራራቢ የሚመስሉ ነገር ግን በጥልቀት ሲመረመሩ በአንድ ድንጋጌ ስር ሊሸፈኑ እንደሚገባ የተመለከቱትን ጽንሰ ሀሳቡን ባለመረዳት ተደራራቢ አድርጎ በመውሰድ ህግ አውጭው ካስቀመጠው ውጭ ክስ ሲቀርብና ውሳኔ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ በቅጣት አጣጣል

ጊዜም የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 184(1-ሀ) በሚደነግገው መሰረት በሞት፣ በእድሜ ልክ ወይም በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት የመጨረሻውን ጣሪያ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ሲመጡ ፍርድ ቤቱ መጀመሪያ ሊቀጣ ያሰበውን ያልቀጣው እንደሆነ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቱን ማክበድ እንደሚገባ የዚሁ ድንጋጌ ሁለተኛ ፓራግራፍ በግልጽ አመልክቶ እያለ ፍርድ ቤቶች በህጉ አግባብ ቅጣት የማይወስኑበት ጊዜ እንዳለ መዝገቦች ይተቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች የተፈጸሙት በቸልተኛነት በሆነ ጊዜ ቅጣት ሲጣል ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣው ተወስዶ ሌሎቹ እንደ ቅጣት ማክበጃ እንደሚወሰዱ የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 187(2-ለ) ስር የተመለከተ ቢሆንም ይህን ባለመገንዘብ ቅጣት በመደመር ስሌት ሲወሰን ይስተዋላል፡፡ በተደራራቢ ወንጀሎች ላይ ጽንሰ ሀሳብ፣ ክስ አመሰራረትና ቅጣት አጣጣል ዙሪያ በባለሙያዎች ዘንድ የሚታዩ የግንዛቤ እጥረቶችን ለመፍታት ባለሙያዎች ተከታታይ የሆነ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡